ሦስተኛው

የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት

መግቢያ

ሦስተኛው የዮሐንስ መልእክት የተጻፈው “በሽማግሌው ሐዋርያ በዮሐንስ” ሲሆን ፥ የተጻፈ ውም ጋይዮስ ለተባለ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር ፤ ጸሐፊው በእንድ በኩል ሌሎችን ክርስቲያ ኖች በመርዳቱ ጋይዮስን ያመሰግነዋል ፤ በሌላ በኩል ዲዮጥራጢስ ከተባለ ተንኰለኛ ሰው እን ዲጠነቀቅ ያሳስበዋል ።

---

1 በእውነት ለማፈቅረው ፥ ለተወደደው ጋይ
ዮስ ፤
ከእኔ ከሽማግሌው የተላከ መልእክት ።
2 ወዳጄ ሆይ! በነፍስህ ደኅና እንደሆንህ
ዐውቃለሁ ፤ እንዲሁም ኑርህ ሁሉ እንዲሳካል
ህና ጤንነትም እንዲኖርህ እጸልይልሃለሁ ።
3 አንዳንድ ወንድሞች መጥተው ለእውነት
ታማኝ መሆንህንና እውነትን ይዘህ መኖርህን
ሲመሰክሩ በመስማቴ በጣም ደስ አለኝ ። 4 ምክ
ንያቱም ልጆቼ እውነትን ይዘው መኖራቸውን
ከመስማት ይልቅ ፥ ሌላ ይበልጥ የሚያስደስተኝ
ነገር የለም ።

ጋይዮስ ተመሰከረለት

5 ወዳጄ ሆይ! ምንም እንኳ እንግዶች
ቢሆኑ ለወንድሞች በታማኝነት ትሠራለህ ።
6 እነርሱም ስለ አደረግህላቸው የፍቅር ሥራ
በአማኞች ማኅበር ፊት መስክረዋል ፤ አሁንም
እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ በጕዞአ
ቸው ብትረዳቸው መልካም ነው ። 7 እነርሱ
ክርስቶስን ለማገልገል ሲወጡ ከአረማውያን
ምንም ዕርዳታ አላገኙም ። 8 የእውነት ሥራ
ተካፋዮች እንድንሆን ፥ እንደእነዚህ ያሉትን
ሰዎች መርዳት አለብን ።

ዲዮትሬፌስ ተወቀሰ ፥ ድሜጥሮስ ተመሰገነ

9 ከዚህ በፊት ለቤተ ክርስቲያን ደብዳቤ
ጽፌአለሁ ፤ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪ
መሆን የሚፈልገው ዲዮትሬፌስ አሳቤን አልተ
ቀበለም ። 10 ስለዚህ ወደ እናንተ ስመጣ እርሱ
እየሰደበንና እያዋረደን ያደረገውን ክፉ ሥራ
ሁሉ ፥ ለሁሉም እናገራለሁ ፤ እርሱ የሚያደር
ገው ይህን ብቻ አይደለም ። እርሱ ራሱ ወንድ
ሞችን አይቀበልም ። ሌሎችም እንዳይቀበሉአ
ቸው ይከለክላል ። ከቤተ ክርስቲያንም ያስወጣ
ቸዋል ።
11 ወዳጄ ሆይ! ደጉን ምሰል እንጂ ክፉውን
አትምሰል ። ደግ ሥራ የሚሠራ ሁሉ የእግዚአ
ብሔር ነው ። ክፉ ሥራ የሚሠራ ግን እግዚአብ
ሔርን አላየውም ።
12 ለድሜጥሮስ ሰው ሁሉ በመልካም ይመሰ
ክርለታል ። እውነት ራስዋም ትመሰክርለታ
ለች ። እኛም እንመሰክርለታለን ፤ የእኛም ምስ
ክርነት እውነት መሆኑን ታውቃለህ ።

የመጨረሻ ሰላምታ

13 ልጽፍልህ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበ
ረኝ ፤ ነገር ግን በደብዳቤ ልገልጽልህ አልፈል
ግም ። 14 በቅርቡ ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ ፤
በዚያን ጊዜ ፊትን ለፊትን እንነጋገራ
ለን ።
15 ሰላም ለአንተ ይሁን ።
ወዳጆች ሰላምታ ያቀርቡልሃል ። አንተም
ለወዳጆቻችን አንድ በአንድ ሰላምታ አቅርብ
ልን ።

---

1 ፡- ሐሥ. 19፡29 ፤ ሮም 16፡23 ፤ 1ቆሮ. 1፡14 ።

የይሁዳ መልእክት

መግቢያ

የይሁዳ መልእክት የተጻፈው ፥ አማኞች ሳይሆኑ አማኞች መስለው የሐሰት ትምህርት ከሚ ያሰራጩ ሰዎች ክርስቲያኖችን ለማስጠንቀቅ ነው ፤ በይዘቱ ሁለተኛ ጴጥሮስን በሚመስለው በዚህ አጭር መልእክት ጸሐፊው “በማያጸግም ሁኔታ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠው እምነት በብርቱ እንዲጋደሉ” አንባቢዎቹን በጥብቅ ያሳስባል ።

---

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና የያዕቆብ
ወንድም ከሆነው ከይሁዳ ፥
ለተጠራችሁት ፥ በእግዚአብሔር አብ ለተወ
ደዳችሁት ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠበቃችሁት
ሁሉ ፤
2 ምሕረትና ሰላም ፍቅርም ይብዛላችሁ ።

ሐሰተኞች መምህራን

3 ወዳጆች ሆይ! ስለ ጋራ ደኅንነታችን ልጽ
ፍላችሁ በብርቱ ፈልጌ ነበር ፤ አሁንም በማያዳ
ግም ሁኔታ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠው
እምነት በብርቱ እንድትጋደሉ ለመምከር ልጽ
ፍላችሁ ግድ ሆነብኝ ። 4 የሚፈረድባቸው
መሆኑ ከብዙ ጊዜ በፊት የተጻፈባቸው አንዳ
ንድ ሰዎች ወደ እናንተ ሾልከው ገብተዋል ፤
እነርሱ የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኛነት የሚለ
ውጡ ኃጢአተኞች ናቸው ፤ እርሱ ብቻ ገዥያ
ችንና ጌታችን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስንም
ይክዳሉ ።
5 ምንም እንኳ ይህን ሁሉ አስቀድማችሁ
የምታውቁት ቢሆንም ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን
ከግብጽ አገር አውጥቶ እንዳዳነና ያላመኑትንም
በኋላ እንዳጠፋቸው ላስታውሳችሁ እወዳለሁ ።
6 እንዲሁም ማዕርጋቸውን ባለመጠበቅ ስፍራቸ
ውን የተዉትን መላእክት አስታውሱ ፤ እነርሱን
እግዚአብሔር እስከ ታላቁ የፍርድ ቀን ድረስ
በዘላለም እስራት ፥ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ
ጠብቆ አቆይቷቸዋል ። 7 በዚሁ ዐይነት ሰዶምና
ገሞራ በዙሪያቸው ያሉ ከተሞችም የዝሙት
ኃጢአት ፈጸሙ ፤ የተፈጥሮ ሥርዓትንም በመለ
ወጥ በግብረ ሥጋ ተገናኙ ። ስለዚህ እነርሱ በዘ
ላለም እሳት ለሚቀጡት ምሳሌ ሆነዋል ።
8 እንዲሁም እነዚህ ሰዎች በሕልም እየተ
መሩ ሥጋቸውን ያረክሳሉ ፤ የእግዚአብሔርንም
ሥልጣን ይንቃሉ ፤ በሰማይ ክብር ያላቸውንም
ይነቅፋሉ ። 9 የመላእክት አለቃ ሚካኤል እንኳ
ስለ ሙሴ አስከሬን ከዲያብሎስ ጋር በብርቱ በተ
ከራከረ ጊዜ “እግዚአብሔር ይገሥጽህ!” አለው
እንጂ የስድብ ቃል በመናገር ሊፈርድበት አልደ
ፈረም ። 10 እነዚህ ሰዎች ግን ስማስተዋል ያቃታ
ቸውን ነገር ሁሉ ይሳደባሉ ፤ አእምሮ እንደሌላ
ቸው እንስሶች በተፈጥሮ ስሜት የሚያውቁት
ነገር ቢኖር እንኳ በእርሱ ይጠፋሉ ። 11 በቃየል
መንገድ ስለሄዱ ፥ ለገንዘብ ብለው በበለዓም ስሕ
ተት ስለ ወደቁ ፥ ቆራሕ እንደተቃወመ በመቃ
ወማቸው ስለ ጠፉ ወዮላቸው! 12 እነዚህ ሰዎች
ያለ ሐፍረት እየተዳሩ በፍቅር ግብዣችሁ ላይ
ሲገኙ እንቅፋት ይሆኑባችኋል ፤ እነርሱ የሚያስ
ቡት ስለ ራሳቸው ብቻ ነው ፤ በነፋስ እንደሚ
ገፋ ፥ ዝናብ እንደሌለው ደመና ናቸው ። በፍሬ
ወራት እንኳ ፍሬ እንደማይገኝበት ፥ ከሥሩ እን
ደተነቀለና ሁለት ጊዜ እንደሞተ ዛፍ ናቸው ።
13 የአሳፋሪ ድርጊታቸውን ዐረፋ የሚደፍቁ ፥
እንደ ተቁጣ የባሕር ማዕበል ናቸው ፤ ድቅድቅ
ጨለማ ለዘላለም የሚጠብቃቸው ፥ እንደሚንከራ
ተቱ ከከቦች ናቸው ።
14 ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ ትውልድ የሆነው
ሔኖክ ስለነዚህ ሰዎች እንዲህ ሲል ትንቢት
ተናግሮአል ፥ “እነሆ ጌታ ከብዙ ሺ ቅዱሳን
ጋር ይመጣል ። 15 የሚመጣውም በሰው ሁሉ
ላይ ሊፈርድ ዐመፀኞችንና ኃጢአተኞችን ሁሉ
በዐመፃ ሥራቸው ሁሉና በእግዚአብሔር ላይ
በተናገሩት የስድብ ቃል ሁሉ ሊወቅስ ነው ።”
16 እነዚህ ሰዎች ሁልጊዜ የሚያጉረመር
ሙና በምንም ነገር የማይደሰቱ ናቸው ፤ የራሳ
ቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ናቸው ፤ አፋ
ቸው በትዕቢት ቃል የተሞላ ነው ፤ የራሳቸውን
ጥቅም በመፈለግ ሰውን ይለማመጣሉ ።

---

1 ፡- ማቴ. 13፡55 ፤ ማር. 6፡3 ። 5 ፡- ዘኍ. 12፡51 ፤ ዘጸ. 14፡29-30 ። 7 ፡- ዘፍ. 19፡1-24 ። 9 ፡- ዘኁ. 10፡13 ፤21 ፤ 12፡1 ፤ ራእ. 12፡7 ፤ ዘዳ. 34፡6 ፤ ዘካ. 3፡2 ። 11 ፡- ዘፍ. 4፡3-8 ፤ ዘጸ. 22፡1-35 ፤ 16፡1-35 ። 14 ፡- ዘፍ. 5፡18 ፤21-24 ።

ማስጠንቀቂያና ምክር

[17]እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ! የጌታችን የኢ.
የሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ከዚህ በፊት የተናገሩ
ትን ቃል አስታውሱ ። [18]እነርሱ “በመጨረ
ሻው ዘመን የገዛ ራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከ
ተሉ ዘባኞች ይመጣሉ” ብለዋችሁ ነበር ።
[19]እነርሱ ሰውን የሚለያዩ ፥ የሥጋን ምኞት
የሚከተሉ መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ሰዎች
ናቸው ። [20]እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ! ከሁሉ
በላይ በተቀደሰው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማ
ነጽ ትጉ ። በመንፈስ ቅዱስም ኀይል ጸልዩ ።
[21]ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በምሕረቱ የዘላ
ለም ሕይወት እንዲሰጣችሁ በመጠባበቅ ራሳች
ሁን በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ጠብቁት ።

[22]ለሚጠራጠሩ ሰዎች ርኅራኄ አድርጉላ
ቸው ፤ [23]አንዳንዶችን ከእሳት እውጥታችሁ
አድኑአቸው ፤ ሌሎችን በፍርሃት ራሩላቸው ፤
ሆኖም በኃጢአት የረከሰውን ሰውነታቸውን የነ
ካውን ልብስ እንኳ ሳይቀር ጥሉ ።

የምስጋና ጸሎት

[24]እንዳትወድቁ ሊያደርጋችሁና ያለ ነቀ
ፋም አድርጎ በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባ
ችሁ ለሚችል ፥ [25]እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆ
ነው አምላክ ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
አማካይነት ከጥንት ጀምሮ ፥ አሁንም ፥ ለዘላለ
ምም ክብርና ግርማ ፥ ኀይልና ሥልጣንም
ይሁን! አሜን ።

የዮሐንስ ራእይ

መግቢያ

የዮሐንስ ራእይ የተጻፈው ክርስቲያናት ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታቸው አድርገው በቅድስና በመኖራቸው ምክንያት ስደትና መከራ ይደርስባቸው በነበረ ጊዜ ነው ፤ የጸሐፊው ዋና ትኩረት አንባቢዎቹ ተስፋቸው ሙሉ እንዲሆን ለማበረታታትና በደረሰባቸው ስደትና መከራ ውስጥ በእምነታቸው እንዲጸኑ ለማደፋፈር ነው ።

የመጽሐፉ አብዛኛው ክፍል ብዛት ያላቸውና ተከታታይ የሆኑ ራእዮችን የያዘ ሲሆን ፥ ራእዮቹም በዚያን ዘመን የነበሩ ምእመናን ሊረዱአቸው የሚችሉ ፥ ለሌሎች ግን ምስጢር ሆነው የሚቆዩ በሥዕላዊ አነጋገር የቀረቡ ናቸው ፤ የመዝሙር አዝማች እንደሚደጋገመው ዐይነት የዚህም መጽሐፍ ርዕሶች በተለያዩት ራእዮች አማካይነት በተለያየ መልክ ተደጋግመው ቀርበዋል ፤ ስለ መጽሐፉ አተረጓጐም የተለያየ አሳብ ያለ ቢሆንም ማእከላዊው አሳብ ግልጥ ነው ፤ ይኸውም “እግዚአብሔር ፥ ጌታ በሆነው በክርስቶስ አማካይነት በማያዳግም ሁኔታ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሰይጣንን ጭምር ጠላቶቹን ሁሉ ድል ይነሣል ፤ ድሉም በተጠናቀቀ ጊዜ ታማኞች ለሆኑት ወገኖቹ የአዲስ ሰማይንና የአዲስ ምድርን በረከት ያወርሳቸዋል” የሚለው ነው ።

ምዕራፍ 1

[1]ይህ ራእይ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚሆነውን
ነገር ለአገልጋዮቹ እንዲያሳያቸው እግዚአብሔር
ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ነው ፤ ኢየሱስ ክርስ
ቶስም መልአኩን ልኮ ለአገልጋዩ ለዮሐንስ ይህን
ራእይ ገለጠለት ። [2]ዮሐንስም እንዳየው ሁሉ
የእግዚአብሔርን ቃልና የኢየሱስ ክርስቶስን
ምስክርነት ተናግሮአል ። [3]ይህ ሁሉ የሚፈጸም
በት ጊዜ ቅርብ ስለሆነ ይህን የትንቢት መጽሐፍ
የሚያነብ የተባረከ ነው ፤ እንዲሁም የትንቢቱን
ቃል የሚሰሙና በመጽሐፉም ውስጥ የተጻፈ
ውን የሚፈጽሙ የተባረኩ ናቸው ።

ለሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት የተላከ ሰላምታ

[4-5]ከዮሐንስ ለሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲ
ያናት የተላከ ሰላምታ ፥

ካለው ፥ ከነበረው ፥ ከሚመጣው ከእግዚአብ
ሔር ፥ በዙፋኑ ፊት ካሉት ከሰባቱ መንፈሶ
ችም ፥ ታማኝ ምስክር ከሆነው ፥ ከሞት በመነ
ሣት በኵር ከሆነው ፥ የምድር ነገሥታት ገዥ

18 ፡- 2ጴጥ. 3፡3 ።
1፡4 ፡- ዘጸ. 3፡14 ፡ ራእ. 4፡5 ። 1፡5 ፡- ኢሳ. 55፡4 ፡ መዝ. 89፡27 ።

ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ፥ ጸጋና ሰላም ለእና
ንተ ይሁን ። ለወደደን ፥ በደሙም ከኃጢአታ
ችን ለዋጀን ፥ [6]አባቱ የሆነውን አምላክ እንድና
ገለግል የካህናት መንግሥት ሳደረገን ፥ ለኢየሱስ
ክርስቶስ ክብርና ኀይል ለዘላለም ይሁን ፤
አሜን ።

[7]እነሆ በደመና ይመጣል ፤ የወጉት ሰዎች
እንኳ ሳይቀሩ ሰው ሁሉ ያየዋል ፤ የምድርም
ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ ምክንያት ያለቅሳሉ ፤
አዎ! ይህ ነገር እውነት ነው ፤ አሜን ።

[8]ያለው ፥ የነበረው ፥ የሚመጣውም ሁሉን
የሚችል እግዚአብሔር አምላክ “አልፋና
ዖሜጋ ፥ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ
ነኝ” ይላል ።

የክርስቶስ በራእይ መገለጥ

[9]በኢየሱስ ክርስቶስ ባለን ኅብረት ፥ የመንግ
ሥቱ ወራሾች ከሆናችሁ ከእናንተ ጋር የመከ
ራና የትዕግሥት ተካፋይ የሆንሁ እኔ ወንድማ
ችሁ ዮሐንስ ፥ በእግዚአብሔር ቃልና በኢየሱስ
ምስክርነት ምክንያት ፍጥሞ በምትባል ደሴት
ነበርሁ ፤ [10]በጌታ ቀን በመንፈስ ተመስጦ ሳይ
ሳለሁ የመለከት ድምፅ የሚመስል ታላቅ ድምፅ
ከበስተኋላዬ እንዲህ ሲል ሰማሁ ፤ [11]“የምታየ
ውን በመጽሐፍ ጽፈህ ወደ ሰባቱ አብያተ ክር
ስቲያናት ፥ ማለትም ወደ ኤፌሶን ፥ ወደ ሰምር
ኔስ ፥ ወደ ጴርጋሞን ፥ ወደ ትያጥሮን ፥ ወደ
ሰርዴስ ፥ ወደ ፊላደልፍያና ወደ ሎዶቅያ
ላክ ።”

[12]ማን እንደተናገረኝ ለማወቅ ወደ ኋላዬ
ዞር አልሁ ፤ ዞር ባልሁ ጊዜም ሰባት የወርቅ
መቅረዞችን አየሁ ፤ [13]በመቅረዞቹ መካከል
የሰው ልጅ የሚመስለውን አየሁ ፤ እርሱ እስከ
እግሩ የሚደርስ ረዥም ልብስ የለበሰ ፥ ደረቱን
በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበረ ። [14]ራሱና
የራስ ጠጉሩ እንደ ነጭ የበግ ጠጕርና እንደ
በረዶ ነጭ ነበሩ ፤ ዐይኖቹም እንደ እሳት ነበል
ባል ነበሩ ፤ [15]እግሮቹም በእሳት ቀልጦ እንደነ
ጠረ ናስ ይመስሉ ነበር ፤ ድምፁም እንደ ታላቅ
የፏፏቴ ውሃ ድምፅ ነበረ ፤ [16]በቀኝ እጁ ሰባት
ከዋክብት ይዞ ነበር ፤ ከሁለት በኩል ስለት ያለው
ሰይፍ ከአፉ ይወጣ ነበር ፤ ፊቱም በሙሉ ድም
ቀቱ እንደሚያበራ ፀሐይ ነበረ ። [17]ባየሁትም
ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ በእግሩ ሥር ወደ
ቅሁ ፤ እርሱ ግን ቀኝ እጁን በላዬ ጭኖ እንዲህ
አለኝ ፥ “አትፍራ ፤ የመጀመሪያውና የመጨረ
ሻው እኔ ነኝ ፤ [18]ሕያውም ነኝ ፤ ሞቼ ነበር ፥
ነገር ግን እነሆ ለዘላለም ሕያው ነኝ ፤ በሞትና
በሲኦል ላይ ሥልጣን አለኝ ። [19]እንግዲህ ያየኸ
ውን ፤ አሁን ያለውንና በኋላ የሚመጣውን
ጻፍ ። [20]በቀኝ እጄ ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክቦችና
የሰባቱም የወርቅ መቅረዞች ምስጢር ይህ
ነው ፤ ሰባቱ ከዋክቦች የሰባቱ አብያተ ክርስቲያ
ናት መላእክት ናቸው ፤ ሰባቱ መቅረዞችም
ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ።

ምዕራፍ 2

(1) የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን

[1]“ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መልአክ እን
ዲህ ብለህ ጻፍ ፥

“ይህም ሰባቱን ኮከቦች በቀኝ እጁ ከያዘውና
በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል ከሚመላለ
ሰው የተነገረ ነው ፤ [2]ሥራህን ፥ ጥረትህን ፥ ትዕ
ግሥትህን ዐውቃለሁ ፤ ክፉዎችን ልትታገሣ
ቸው እንዳልፈቀድህ ፥ ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋር
ያት ነን የሚሉትን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው
እንዳገኘሃቸው ዐውቃለሁ ። [3]በትዕግሥት መጽ
ናትህንና ስለ ስሜም ሳትሰለች መከራ መቀበል
ህን ዐውቃለሁ ፤ [4]ነገር ግን አንድ የምነቅፍብህ
ነገር አለኝ ፤ ይኸውም የቀድሞውን ፍቅርህን
ትተሃል ፥ [5]ከመውደቅህ በፊት የት እንደነበርህ
አስታውስ ፤ ንስሐም ግባ ፤ በመጀመሪያ ታደር
ገው የነበረውን ሥራህን አድርግ ፤ ይህን ሁሉ
ባታደርግ ግን ወደ አንተ እመጣለሁ ፤ ንስሐም
ካልገባህ መቅረዝህን ከስፍራው አነሣዋለሁ ።
[6]ነገር ግን የሚያስመሰግንህ አንድ ነገር አለ ፤
ይህም እኔ የምጠላውን የኒቆላውያንን ሥራ
ጠልተሃል ።

[7]“መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለ
ውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ! ድል ለነሣ በእግ
ዚአብሔር ገነት ውስጥ ካለው ከሕይወት ዛፍ
ፍሬ እንዲበላ አደርገዋለሁ ።

(2) የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን

[8]“ለሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እን
ዲህ ብለህ ጻፍ ፥

“ይህም ፥ የመጀመሪያና የመጨረሻ ከሆ
ነው ፤ ሞቶ ከነበረውና ሕያው ከሆነው የተነገረ
ነው ፤ [9]መከራህንና ድኽነትህን ዐውቃለሁ ፤
ይሁን እንጂ ሀብታም ነህ ፤ አይሁዳውያን ሳይ
ሆኑ አይሁዳውያን ነን የሚሉ ፤ የሰይጣን ማኅ
በር የሆኑ ፥ ስምህን እንዳጠፉት ዐውቃለሁ ፤
[10]ወደ ፊት የሚደርስብህን መከራ አትፍራ ፤
እነሆ እንድትፈተኑ ከእናንተ አንዳንዶቹን ዲያ
ብሎስ ወደ እስር ቤት ያገባችኋል ፤ ዐሥር

1፡6 ፡- ዘጸ. 19፡6 ፡ ራእ. 5፡10 ። 1፡7 ፡- ዳን. 7ቀ13 ፡ ማቴ. 24፡30 ፡ ማር. 13፡26 ፡ ሉቃ. 21፡27 ፡ 1ተሰ. 4፡17 ፡ ዘኁ. 12፡10 ፡ ዮሐ. 19፡34 ፡37 ። 1፡8 ፡- ራእ. 22፡13 ፡ ዘጸ. 3፡14 ። 1፡13 ፡- ዳን. 7፡13 ፡ 10፡5 ። 1፡14-15 ፡- ዳን. 7፡9 ፡ 10፡6 ። 1፡15 ፡- ሕዝ. 1፡24 ፡ 43፡2 ። 1፡17 ፡- ኢሳ. 44፡6 ፡ 48፡12 ፡ ራእ. 2፡8 ፡ 22፡13 ። 2፡7 ፡- ዘፍ. 2፡9 ፡ ራእ. 22፡2 ፡ ሕዝ. 28፡13 ፡ 31፡8 ። 2፡8 ፡- ኢሳ. 44፡6 ፡ 48፡12 ፡ ራእ. 1፡17 ፡ 22፡13 ።

ቀንም መከራ ትቀበላላችሁ ፤ እስከ ሞት ድረስ
ታማኝ ሁን ፤ የሕይወት አክሊል እሰጥሃለሁ ።
11 “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለ
ውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!
“ድል የነሣ በሁለተኛው ሞት አይጐዳም ።

(3) የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን

12 “ለጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን መልአክ
እንዲህ ብለህ ጻፍ ፥
“ይህም ፥ በሁለት በኩል ስለት ያለውን
ሰይፍ ከያዘው የተነገረ ነው ፤ 13 አንተ ፥ የሰይ
ጣን ዙፋን ባለበት ስፍራ መኖርህን ዐውቃ
ለሁ ፤ ይሁን እንጂ ስሜን አጥብቀህ ይዘሃል ፤
ሃይማኖትህን አልካድህም ፤ ታማኝ ምስክሬ የነ
በረው አንቲጳስ ሰይጣን በሚኖርበት በእናንተ
ከተማ በተገደለ ጊዜ እንኳ በእኔ ማመንህን አል
ተውህም ። 14 ነገር ግን የምንቅፍብህ አንዳንድ
ነገሮች አሉኝ ፤ ይኸውም የበለዓምን ትምህርት
የያዙ አንዳንድ ሰዎች በመካከላችሁ አሉ ፤ ይህ
በለዓም የእስራኤል ሕዝብ ለጣዖት የተሠዋውን
በመብላትና ዝሙት በማድረግ እንዲሰናከሉ ባላ
ቅን የመከረ ነው ። 15 እንዲሁም የኒቆላውያንን
ትምህርት የያዙ ሰዎችም በመካከላችሁ አሉ ፤
16 ስለዚህ ንስሓ ግባ! አለበለዚያ በቶሎ ወደ
አንተ መጥቼ ከአፌ በሚወጣው ሰይፍ እወጋቸ
ዋለሁ ።
17 “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለ
ውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ! ድል ለነሣ ከተሰ
ወረው መና እሰጠዋለሁ ፤ አዲስ ስም የተጻፈበ
ትን ነጭ ድንጋይ እሰጠዋለሁ ፤ ከተቀባዩ በቀር
ይህን ሌላ ማንም አያውቀውም ።

(4) የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን

18 “ለትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን መልአክ
እንዲህ ብለህ ጻፍ ፥
“ይህም የእሳት ነበልባል የሚመስሉ ዐይ
ኖች ካሉትና በእሳት ቀልመ የነጠረ ናስ የሚመ
ስሉ እግሮች ካሉት ፥ ከእግዚአብሔር ልጅ የተ
ነገረ ነው ፤ 19 ሥራህንና ፍቅርህን ፥ እምነትህ
ንና አገልግሎትህን በትዕግሥት መጽናትህንም
ዐውቃለሁ ፤ የኋለኛው ሥራህ ከፊተኛው እንደ
ሚበልጥም ዐውቃለሁ ። 20 ነገር ግን አንድ የም
ነቅፍብህ ነገር አለኝ ፤ ይኸውም ‘ነቢይት ነኝ’
የምትለዋን ሴት ፥ ኤልዛቤልን ችላ ብለህ ታግሠ
ሃታል ፤ እርስዋ አገልጋዮቼ እንዲሴስኑና ለጣ
ዖት የተሠዋ ምግብ እንዲበሉ በማስተማር አሳስ
ታቸዋለች ። 21 ንስሓ እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ፤
እርስዋ ግን ከዝሙትዋ ንስሓ መግባትን አልፈለ
ገችም ። 22 ስለዚህ በሥቃይ አልጋ ላይ እጥላታ
ለሁ ፤ ከእርስዋ ጋር ከሠሩት ከክፉ ሥራቸው
ንስሓ ገብተው ካልተመለሱ በቀር ከእርስዋ ጋር
ያመነዘሩትንም ሁሉ ብርቱ ሥቃይ አመጣባቸ
ዋለሁ ፤ 23 ልጆቻዋንም በሞት እቀጣለሁ ፤ አብ
ያተ ክርስቲያናትም ሁሉ የሰውን አሳብና
ምኞት የምመረምር እኔ መሆኔን ያውቃሉ ፤
ለእያንዳንዳችሁም እንደየሥራችሁ እሰጣችኋ
ለሁ ።
24 “በትያጥሮን ላላችሁትና ይህን መጥፎ
ትምህርት ላልተቀበላችሁት ሁሉ ፥ እንዲሁም
አንዳንዶች ‘የሰይጣን ጥልቅ ምስጢር ነው’
የሚሉትን ላልተከተላችሁ ሌላ ሸክም አልጭን
ባችሁም ፤ 25 ሆኖም እኔ እስከመጣ ድረስ ያላች
ሁን አጥብቃችሁ ያዙ እላችኋለሁ ። 26 ድል
ለነሣ ፥ በሥራዬም ላይ እስከ መጨረሻ ጸንና
በሕዝቦች ላይ ሥልጣን እሰጠዋለሁ ፤ 27 ‘በብረ
ትም በትር ይገዛቸዋል ፤ እንደ ሸክላ ዕቃም
ቀጥቅጦ ያደቅቃቸዋል ፥’ ይህም ሥልጣን እኔ
ከአባቴ እንደተቀበልሁት ዐይነት ነው ፤ 28 የንጋ
ትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ ።
29 “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለ
ውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!

ምዕራፍ 3

(5) የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን

1 “ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እን
ዲህ ብለህ ጻፍ ፥
“ይህም ፥ ሰባቱን የእግዚአብሔር መንፈሶ
ችና ሰባቱን ኮከቦች ከያዘው የተነገረ ነው ፤
ሥራህን ዐውቃለሁ ፤ በስም ሕያው ነህ ፤ ነገር
ግን ሞተሃል ። 2 ስለዚህ ንቃ! ሥራህ በእምላኬ
ፊት ፍጹም ሆኖ ስላላገኘሁት ሊሞት የቀረበ
ውን የቀረውን ነገር አጽና ። 3 እንግዲህ ምን
ዐይነት ትምህርት እንደተቀበልህና እንደ ሰማህ
አስታውስ ፤ ጠብቀውም ፤ ንስሓም ግባ ፤ ባት
ነቃ ግን እንደ ሌባ በድንገት እመጣብሃለሁ ፤
በምን ሰዓት ወደ አንተ እንደምመጣ አታው
ቅም ። 4 ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰር
ዴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ጋር አሉ ፤ ከእኔ ጋር
መሄድ የተገባቸው ስለሆኑ ነጭ ልብስ ለብሰው
ከእኔ ጋር ይሄዳሉ ። 5 ድል የነሣ እንደ እነርሱ
ነጭ ልብስ ይለብሳል ፤ ስሙን በአባቴና በመላእ
ክቱም ፊት አስታውቅለታለሁ ፤ የሕያዋን ስም
ከሚመዘገብበት ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስ
ሰውም ።
6 “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለ
ውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!

3:7 ፡- ኢሳ. 22:22 ፡ ኢዮብ 12:14 ። 3:9 ፡- ኤሳ. 49:23 ፡ 60:14 ፡ 43:4 ። 3:12 ፡- ራእ. 21:2 ፡ ኢሳ. 62:2 ፡ 65:15 ። 3:14 ፡- ምሳ. 8:22 ። 3:19 ፡- ምሳ. 3:12 ፡ ዕብ. 12:6 ። 4:2-3 ፡- ሕዝ. 1:26-28 ፡ 10:1 ። 4:5 ፡- ዘጸ. 19:16 ፡ ራእ. 8:5 ፡ 11:19 ፡ 16:18 ፡ ሕዝ. 1:13 ፡ ራእ. 1:4 ፡ ዘካ. 4:2 ። 4:6-7 ፡- ሕዝ. 1:22 ፡5-10 ፡ 10:14 ። 4:8 ፡- ሕዝ. 1:18 ፡ 10:12 ፡ ኢሳ. 6:2-3 ።

(6) የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን

7 “ለፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን መልአክ
እንዲህ ብለህ ጻፍ ፥
“ይህም ፥ ቅዱስና እውነተኛ ከሆነው ፥ የዳ
ዊትን መክፈቻ ቍልፍ ከያዘው የተነገረ ነው ፤
እርሱ የሚከፍተውን ማንም አይዘጋውም ፤
እርሱ የሚዘጋውንም ማንም አይከፍተውም ።
8 ሥራህን ዐውቃለሁ ፤ እነሆ! ማንም ሊዘጋው
የማይችለውን የተከፈተ በር በፊትህ አድርጌልሃ
ለሁ ፤ ኀይልህ ትንሽ መሆኑን ዐውቃለሁ ፤
ይሁን እንጂ ቃሌን ጠብቀሃል ፤ ስሜንም አልካ
ድህም ። 9 እንግዲህ አይሁዳውያን ሳይሆኑ አይ
ሁዳውያን ነን የሚሉትን እነዚያን ከሰይጣን
ማኅበር የሆኑትን ውሸታሞች መጥተው በእግ
ርህ ሥር እንዲወድቁ አደርጋቸዋለሁ ፤ እኔ
እንደ ወደድሁህም እንዲያውቁ አደርጋቸዋ
ለሁ ። 10 ‘ትዕግሥተኛ ሁን’ ያልሁህን ቃሌን
ስለጠበቅህ ፥ እኔም በምድር ላይ የሚኖሩትን
ሊፈትኗቸው በዓለም ሁሉ ላይ ከሚመጣው
ከመከራ ሰዓት አድንሃለሁ ። 11 እነሆ በቶሎ
እመጣለሁ! አክሊልህን ማንም እንዳይወስድብህ
ያለህን አጥብቀህ ያዝ ። 12 ድል የነሣውን በአም
ላኬ ቤተ መቅደስ ዐምድ አደርገዋለሁ ፤ ከዚ
ያም ከቶ አይወጣም ፤ የአምላኬን ስምና የአም
ላኬን ከተማ ስም በእርሱ ላይ እጽፋለሁ ፤ ይህ
ችም ከተማ ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወር
ደው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት ፤ የእኔንም
አዲስ ስም በእርሱ ላይ እጽፋለሁ ።
13 “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለ
ውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!

(7) የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን

14 “ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እን
ዲህ ብለህ ጻፍ ፥
“ይህም ፥ አሜን ከሆነው ፥ ታማኝና እውነ
ተኛ ምስክር ከሆነው ፥ ለእግዚአብሔር ፍጥረት
ሁሉ መጀመሪያ ከሆነው የተነገረ ነው ፤ 15 ሥራህን
ዐውቃለሁ ፤ በራድ ወይም ትኩስ አይደለህም ፤
በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንማ መልካም በሆነ
ነበር ፤ 16 በራድ ወይም ትኩስ ሳትሆን ሰብ
ያልህ ስለሆንህ ፥ ከአፌ አውጥቼ ልተፋህ ነው ፤
17 ‘እኔ ሀብታም ነኝ ፤ ብዙ ሀብት አለኝ ፤
የሚጐድለኝ ምንም የለም’ ትላለህ ፤ ነገር ግን
ጕስቋላ ፥ ምስኪን ፥ ድኻ ፥ ዕውር ፥ የተራቆት
ህም መሆንህን አታውቅም ፤ 18 ሀብታም ለመ
ሆን በእሳት የተፈተነውን ወርቅ ከእኔ እንድት
ገዛ ፥ የራቁትነትህን ሐፍረት ለመሸፈን ነጭ
ልብስ እንድትለብስ ፥ ለማየትም ዐይንህን እን
ድትኳል እመክርሃለሁ ። 19 እኔ የምወዳቸውን
ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ ፤ እቀጣቸዋለሁም ፤ ስለ
ዚህ ትጋ! ንስሓም ግባ ፤ 20 እነሆ እኔ በበር
ቆሜ አንኳኳለሁ ፤ ማንም ድምፄን ሰምቶ በሩን
ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ ገብቼ ከእርሱ ጋር እበ
ላለሁ ፤ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል ፤ 21 እኔ
ድል ነሥቼ ከአባቴ ጋር በአባቴ ዙፋን ላይ
እንደ ተቀመጥሁ ፥ እንዲሁም ድል የነሣ ከእኔ
ጋር በዙፋኔ ላይ እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ ።
22 “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለ
ውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!”

ምዕራፍ 4

የእግዚአብሔር ዙፋንና ሰማያዊው
የጸሎት ሥነ ሥርዓት

1 ከዚህ በኋላ እነሆ የተከፈተ በር በሰማይ
አየሁ ፤
እንደ መለከት ድምፅ ሆኖ ሲናገር የሰማሁት
የመጀመሪያው ድምፅ “ና ወደዚህ ውጣ! ወደ
ፊት መሆን የሚገባቸውን ነገሮች አሳይሃለሁ”
አለኝ ፤ 2 ወዲያውኑ በመንፈስ ተመሰጥሁ ፤
እነሆ በሰማይ ዙፋን ተዘርግቶ አየሁ ፤ 3 በዙ
ፋኑ ላይ ተቀምጦ የነበረው መልኩ የኢያስጲድ
ንና የሰርዲናን ዕንቊ ይመስል ነበር ፤ በዙፋ
ኑም ዙሪያ የመረግድ ዕንቊ የመሰለ ቀስት
ደመና ነበረ ፤ 4 እንዲሁም በዙፋኑ ዙሪያ ሃያ
አራት ዙፋኖች ነበሩ ፤ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ
ልብስ የለበሱና በራሳቸው ላይ የወርቅ አክሊል
የደፉ ሃያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው
ነበር ። 5 ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓ
ድም ይወጡ ነበር ፤ በዙፋኑ ፊት የሚበሩ
ሰባት ችቦዎች ነበሩ ፤ እነርሱ ሰባቱ የእግዚአብ
ሔር መንፈሶች ናቸው ። 6 በዙፋኑ ፊት ጥርት
ያለ የሚያንጸባርቅ የመስተዋት ባሕር ነበረ ።
በመካከል ፥ በዙፋኑ ዙሪያ በስተፊትና በስተኋላ
ብዙ ዐይኖች ያሉአቸው አራት እንስሶች
ነበሩ ። 7 የመጀመሪያው እንስሳ አንበሳ ይመስል
ነበር ፤ ሁለተኛው በሬ ይመስል ነበር ፤ ሦስተ
ኛው የሰው ፊት የሚመስል ፊት ነበረው ፤ አራ
ተኛው የሚበርር ንስር ይመስል ነበር ። 8 አራ
ቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች
ነበሩአቸው ፤ በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዐይ
ኖች ሞልተውባቸዋል ፤ ሌሊትና ቀን ፦
“ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ
ሁሉን የሚችል ጌታ አምላክ ፥
የነበረና ያለ ፥ የሚመጣውም”
ከማለት አያቋርጡም ነበር ።

[9]እንስሶቹ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለዘላ
ለም ለሚኖረው ክብር ፥ ውዳሴ ፥ ምስጋና በሚ
ያቀርቡበት ጊዜ ሁሉ ፥ [10]ሃያ አራቱ ሽማግሌ
ዎች ዘላለም በሚኖረው ፥ በዙፋኑ ላይ በተቀመ
ጠው ፊት በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዳሉ ፤
አክሊሎቻቸውንም በዙፋኑ ፊት አኑረው ፥
[11] “ጌታችንና አምላካችን ሆይ!
ሁሉን ነገር ስለፈጠርህ ፥
ሁሉም ነገር የተፈጠረውና
መሆንን ያገኘው በአንተ ፈቃድ
ስለሆነ
ክብርና ውዳሴ ኃይልም ለመቀበል
የተገባህ ነህ” ይሉ ነበር ።

ምዕራፍ 5

መጽሐፍና በጉ

[1]በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ቀኝ እጅ ፥ በው
ስጥና በውጭ የተጻፈበት በሰባት ማኅተም የታ
ሸገ መጽሐፍ አየሁ ፤ [2]አንድ ብርቱ መልአክ
በታላቅ ድምፅ “ማኅተሞቹን መፍታትና መጽ
ሐፉን መክፈት የተገባው ማንነው?” ብሎ ሲና
ገር አየሁ ። [3]ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድር
ወይም ከምድር በታች መጽሐፉን መክፈትና
ውስጡን መመልከት የተቻለው ማንም አልነበ
ረም ። [4]መጽሐፉን መክፈትና ውስጡን መመል
ከት የተገባው ስላልተገኘ በጣም አለቀስሁ ፤
[5]በዚያን ጊዜ ከሽማግሌዎቹ አንዱ “አታል
ቅስ ፥ እነሆ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ ፥ የዳ
ዊት ሥር ድል ነሥቶአል ፤ እርሱ መጽሐፉንና
ሰባቱን ማኅተሞች መክፈት ይችላል” አለኝ ።

[6]ከዚህ በኋላ በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች
መካከል ፥ በሽማግሌዎችም መካከል የታረደ
የሚመስል በግ ቆሞ አየሁ ፤ ይህ በግ ሰባት ቀን
ዶችና ሰባት ዐይኖች ነበሩት ፤ እነርሱ ወደ
ዓለም ሁሉ የተላኩ ሰባቱ የእግዚአብሔር መን
ፈሶች ናቸው ። [7]በጉ መጣና በዙፋኑ ላይ ከተ
ቀመጠው ቀኝ እጅ መጽሐፉን ወሰደ ፤ [8]መጽ
ሐፉን በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሃያ አራቱ
ሽማግሌዎች በበጉ ፊት በግንባራቸው ተደፉ ፤
እያንዳንዳቸው በገና ይዘው ነበር ፤ እንዲሁም
የቅዱሳን ጸሎት የሆነው ዕጣን የሞላበትን የወ
ርቅ ሙዳይ ይዘው ነበር ። [9]አዲስ መዝሙርም
እንዲህ እያሉ ዘመሩ ፥
“መጽሐፉን ለመውሰድና
ማኅተሞቹን ለመክፈት የተገባህ
ሆነሃል ፤
ምክንያቱም አንተ ታርደሃል ፤
በደምህም ከየነገዱ ፤ ከየቋንቋው ፥
ከየወገኑ ፥ ከየሕዝቡ ሁሉ
ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሃል ፤
[10] ለአምላካችንም የካህናት መንግሥት
እንዲሆኑ አድርገሃቸዋል ፤
በምድርም ላይ ይነግሣሉ ።”
[11] ስመለከትም በዙፋኑና በእንስሶቹ በሽማግ
ሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ
ሰማሁ ፤ ብዛታቸውም በብዙ ሺና በብዙ ሚሊ
ዮን የሚቈጠር ነበር ፤ [12]በታላቅ ድምፅም ፥
“የታረደው በግ ኃይል ፥ ሀብት ፥
ጥበብ ፥ ብርታት ፥ ክብር ፥ ውዳሴ ፥
ምስጋና ለመቀበል የተገባው ነው”
አሉ ።
[13]በሰማይና በምድር ፥ ከምድር በታችና በባሕር
በእነርሱም ያሉ ፍጥረቶች ሁሉ ፥
“በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለበጉም
ምስጋና ፥ ክብር ፥ ውዳሴ ፥ ኃይል
ለዘላለም ይሁን!” ሲሉ ሰማሁ ።
[14]አራቱ እንስሶችም “አሜን” አሉ ፤ ሽማግሌ
ዎቹም በግንባራቸው ተደፍተው ሰገዱ ።

ምዕራፍ 6

የማኅተሞች መክፈት

[1]ከዚህም በኋላ በጉ ከሰባቱ ማኅተሞች የመ
ጀመሪያውን ሲከፍት አየሁ ። ከአራቱ እንስሶች
አንዱ እንደ ነጐድጓድ በሚያስገመግም ድምፅ
“ና” ሲል ሰማሁ ። [2]እነሆ ነጭ ፈረስ አየሁ
በፈረሱ ላይ የተቀመጠው ቀስት ይዞ ነበር ፤
አክሊልም ተሰጠው ፤ ድል ነሺ ሆኖ ከድል
ወደ ድል ለመሄድ ወጣ ።

[3]በጉ ሁለተኛውን ማኅተም በከፈተ ጊዜ ፥
ሁለተኛው እንስሳ “ና” ሲል ሰማሁ ። [4]ሌላ
ደማቅ ቀይ ፈረስ ወጣ ፤ በፈረሱ ላይ ለተቀመ
ጠው ሰላምን ከምድር እንዲያስወግድና ሰዎች
እርስ በርሳቸው እንዲተላለቁ ለማድረግ ሥል
ጣን ተሰጠው ፤ ትልቅ ሰይፍም ተሰጠው ።

[5]ሦስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ፥ ሦስ
ተኛው እንስሳ “ና” ሲል ሰማሁ ፤ እነሆ ጥቍር
ፈረስ አየሁ ፤ በፈረሱ ላይ የተቀመጠው ሚዛን
በእጁ ይዞ ነበር ፤ [6]ድምፅ ከአራቱ እንስሶች
መካከል የመጣ መሰለኝ ፤ ይህ ድምፅ “አንድ
እርቦ ስንዴ በአንድ ቀን ደመወዝ ፥ ሦስት
እርቦ ገብስ በአንድ ቀን ደመወዝ ይሁን ፤ ዘይት
ንና ወይንን ግን አትጕዳ” ሲል ሰማሁ ።

[7]አራተኛውን ማኅተም በከፈተ ጊዜ የአራተ
ኛውን እንስሳ ድምፅ “ና” ሲል ሰማሁ ፤
[8]እነሆ ግራጫ ፈረስ አየሁ ፤ በፈረሱ ላይ የተቀ
መጠው ስሙ ሞት ይባል ነበር ፤ ሲኦልም ይከ
ተለው ነበር ፤ ሞትና ሲኦልም የምድርን አንድ
አራተኛ እጅ በሞርነት ፥ በራብ ፥ በብርቱ
በሽታ ፥ በምድር አራዊት እንዲገድሉ ሥልጣን
ተሰጣቸው ።

[9]አምስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ ፥ ስለ
እግዚአብሔር ቃልና ስለ ሰጡትም ምስክርነት
የተገደሉትን ሰዎች ነፍሶች ከመሠዊያው በታች
አየሁ ፤ [10]እነርሱ በታላቅ ድምፅ “ቅዱስና እው
ነተኛ ፥ የሁሉም በላይ የሆነህ ጌታ ሆይ! በም
ድር ባሉት ሰዎች ላይ የማትፈርደውና ስለ ደማ
ችንም የማትበቀለው እስከ መቼ ነው!” እያሉ
ጮኹ ። [11]ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣ
ቸው ፤ እንደ እነርሱ ገና የሚገደሉ ፥ እንደእነ
ርሱ አገልጋዮች የሆኑ የጓደኞቻቸውና የወንድ
ሞቻቸው ቍጥር እስኪሞላ ድረስ ጥቂት ጊዜ
ወርፈው እንዲቆዩ ተነገራቸው ።

[12]ከዚህ በኋላ በጉ ስድስተኛውን ማኅተም
በከፈተ ጊዜ ይህን አየሁ ፤ እነሆ ታላቅ የምድር
መናወጥ ሆነ ፤ ፀሐይ እንደ ጥቁር ልብስ ጠቆ
ረች ፤ ጨረቃም በሙሉ እንደ ደም ቀላች ፤
[13] ብርቱ ነፋስ የበለስን ዛፍ ሲያወዛውዝ ያልበሰ
ለው ፍሬ ከዛፉ ላይ እንደሚረግፍ ፥ የሰማይ ኮከ
ቦችም ረገፉ ። [14]ሰማይም እንደ ብራና ተጠቅ
ልሎ ተወገደ ፤ ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስ
ፍራቸው ተወሰዱ ። [15]የምድር ነገሥታት ፥ ገዥ
ዎች ፥ የጦር አለቆች ፥ ሀብታሞች ፥ ኀይለኞች ፥
አገልጋዮችና ጌቶችም ሁሉ በዋሻዎችና በተራራ
ዎች አለቶች ውስጥ ተሸሸጉ ፤ [16]ተራራዎቹንና
አለቶቹንም “በላያችን ውደቁ! በዙፋኑ ላይ ከተ
ቀመጠው ፊት ፥ ከበጉም ቍጣ ሰውሩን! [17]ምክ
ንያቱም ታላቁ የቍጣቸው ቀን መጥቶአል! ማን
መቆም ይችላል?” አሉአቸው ።

ምዕራፍ 7

መቶ አርባ አራት ሺ የእስራኤል ሰዎች

[1]ከዚህ በኋላ አራት መላእክት በአራቱ የም
ድር ማእዘኖች ቆመው አየሁ ፤ እነርሱ በምድ
ርም ሆነ በባሕር ወይም በዛፍ ላይ ምንም
ነፋስ እንዳይነፍስ ከአራቱ አቅጣጫ የሚመጡ
ትን የምድር ነፋሶች ያዙ ። [2]የሕያው አምላክን
ማኅተም የያዘ ሌላ መልአክም ከምሥራቅ
ሲመጣ አየሁ ፤ ምድርንና ባሕርን እንዲጐዱ
ሥልጣን ወደ ተሰጣቸው ወደ አራቱ መላእክት
ድምፁን ከፍ አድርጎ ፥ [3]“በአምላካችን አገልጋ
ዮች ግንባር ላይ ማኅተም እስክናትምባቸው
ድረስ ፥ ምድርንም ሆነ ባሕርን ወይም ዛፎችን
አትጕዱ” ብሎ ጮኸ ። [4]የታተሙትንም ሰዎች
ቍጥር ሰማሁ ፤ ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ የታተ
ሙት ሰዎች ቍጥር መቶ አርባ አራት ሺ
ነበር ። [5]ከይሁዳ ነገድ የታተሙት ፡ሥራ
ሁለት ሺ ፤ ከሮቤል ነገድ ፡ሥራ ሁለት ሺ ፤
ከጋድ ነገድ ፡ሥራ ሁለት ሺ ፤ [6]ከአሴር ነገድ
ፀሥራ ሁለት ሺ ፤ ከንፍታሌም ነገድ ፡ሥራ
ሁለት ሺ ፤ ከምናሴ ነገድ ፡ሥራ ሁለት ሺ ፤
[7]ከስምዖን ነገድ ፡ሥራ ሁለት ሺ ፤ ከሌዊ ነገድ
ፀሥራ ሁለት ሺ ፤ ከይሳኮር ነገድ ፡ሥራ ሁለት
ሺ ፤ [8]ከዛብሎን ነገድ ፡ሥራ ሁለት ሺ ፤ ከዮ
ሴፍ ነገድ ፡ሥራ ሁለት ሺ ፤ ከብንያም ነገድ
ፀሥራ ሁለት ሺ ነበሩ ።

ነጭ ልብስ የለበሱ ብዙ ሕዝቦች

[9]ከዚህ በኋላ እነሆ ማንም ሊቈጥራቸው
የማይችል እጅግ ብዙ ሰዎች አየሁ ፤ እነርሱ
ከሕዝብና ከነገድ ፥ ከወገንና ከቋንቋ ሁሉ የተ
ውጣጡ ነበሩ ፤ ነጭ ልብስ ለብሰው ፥ የዘንባባ
ዝንጣፊ በእጃቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት
ቆመው ነበር ፤ [10]በታላቅ ድምፅ እየጮኹም ፥
“ማዳን በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው
የአምላካችንና የበጉ ነው” ይሉ
ነበር ።
[11] መላእክቱ ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ
በአራቱም እንስሶች ዙሪያ ቆመው ነበር ፤ በዙ
ፋኑ ፊት በግንባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብ
ሔር ሰገዱ ፤ [12]እንዲህም አሉ ፥
“አሜን ፥ ውዳሴ ፥ ክብር ፥ ጥበብ ፥
ምስጋና ፥ ክብር ፥ ኀይል ፥ ብርታት
ለአምላካችን ለዘላለም ይሁን!
አሜን ።”
[13] ከሽማግሌዎቹ አንዱ ወደ እኔ መለስ ብሎ
“እነዚህ ነጭ ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው?
ከወዴትስ መጡ?” አለኝ ።
[14]እኔም “ጌታ ሆይ! አንተ ታውቃለህ”
አልሁት ። እርሱም እንዲህ አለኝ ፥ “እነዚህ
ታላቁን መከራ አልፈው የመጡ ናቸው ፤ ልብሶ
ቸውንም በበጉ ደም አጥበው ነጭ አድርገው
ታል ፤ [15]ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት
ሆነው ሌሊትና ቀን በመቅደሱ ያገለግሉታል ።
በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውም መጠለያቸው ይሆ
ናል ። [16]ከእንግዲህ ወዲህ አይርባቸውም ፤ እይ
ጠማቸውም ፤ ፀሐይ አይመታቸውም ፤ ሙቀት
አያገኛቸውም ፤ [17]ምክንያቱም በዙፋኑ መካ
ከል ያለው በግ እረኛቸው ይሆናል ፤ ወደ ሕይ
ወት ውሃ ምንጭም ይመራቸዋል ፤ እግዚአብ
ሔር እምባን ሁሉ ከዐይናቸው ይጠርግላቸ
ዋል ።”

5:1 ፡- ሕዝ. 2:9-10 ፡ ኢሳ. 29:11 ። 5:5 ፡- ዘፍ. 49:9 ፡ ኢሳ. 11:1,10 ። 5:6 ፡- ኢሳ. 53:7 ፡ ዘካ. 4:10 ።
5:8 ፡- መዝ. 141:2 ። 5:9 ፡- መዝ. 33:3 ፡ 98:1 ፡ ኢሳ. 42:10 ። 5:10 ፡- ዘጸ. 19:6 ፡ ራእ. 1:6 ። 5:11 ፡- ዳን. 7:10 ።
6:2 ፡- ዘካ. 1:8 ፡ 6:3,6 ። 6:4 ፡- ዘካ. 1:8 ፡ 6:2 ። 6:5 ፡- ዘካ. 6:2,6 ። 6:8 ፡- ሕዝ. 14:21 ።

6:12 ፡- ራእ. 11:13 ፡ 16:18 ፡ ኢሳ. 13:10 ፡ ኢዩ. 2:10,31 ፡ 3:15 ፡ ማቴ. 24:29 ፡ ማር. 13:24-25 ፡ ሉቃ. 21:25 ።
6:13-14 ፡- ኢሳ. 34:4 ። 6:14 ፡- ራእ. 16:20 ። 6:15 ፡- ኢሳ. 2:19,21 ። 6:16 ፡- ሆሴዕ 10:8 ፡ ሉቃ. 23:30 ።
6:17 ፡- ኢዩ. 2:11 ፡ ሚል. 3:2 ። 7:1 ፡- ኤር. 49:36 ፡ ዘካ. 7:2 ፡ ዘካ. 6:5 ። 7:3 ፡- ሕዝ. 9:4,6 ።
7:14 ፡- ዘፍ. 12:1 ፡ ማቴ. 24:21 ፡ ማር. 13:19 ። 7:16 ፡- ኢሳ. 49:10 ። 7:17 ፡- መዝ. 23:1 ፡ ሕዝ. 34:23 ፡
መዝ. 23:2 ፡ ኢሳ. 49:10 ፡ 25:8 ።

ምዕራፍ 8

የሰባተኛው ማኅተም መከፈት

[1] በጉ ሰባተኛውን ማኅተም በከፈተ ጊዜ፥
እኩል ሰዓት ያህል በሰማይ ዝምታ ሆነ፥ [2] በእ
ግዚአብሔር ፊት የሚቆሙትንም ሰባቱን መላእ
ክት አየሁ፥ ለእነርሱ ሰባት መለከት ተሰጣ
ቸው።

[3] የወርቅ ጥና የያዘ ሌላ መልአክ መጣና
በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፥ በዙፋኑ ፊት
ባለው የወርቅ መሠዊያ ላይ ከቅዱሳን ጸሎት
ጋር የሚያቀርበው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። [4] የዕ
ጣኑ ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ
ወደ እግዚአብሔር ፊት ወጣ። [5] ከዚህ በኋላ
መልአኩ ጥናውን ይዞ የመሠዊያውን እሳት
ሞላበትና ወደ ምድር ወረወረው። ነጐድጓድ፥
ድምፅ፥ መብረቅ፥ የምድር መናወጥም ሆነ።

የመለከቶቹ መነፋት

[6] ሰባት መለከት የያዙ ሰባቱ መላእክት መለ
ከቶቻቸውን ለመንፋት ተዘጋጁ።

[7] የመጀመሪያው መልአክ መለከቱን ነፋ፥
ደም የተቀላቀለበት እሳትና በረዶ ወደ ምድር
ተጣለ፥ የምድር ሢሶ ተቃጠለ፥ የዛፎችም ሢሶ
ተቃጠለ፥ የለመለመ ሣርም ሁሉ ተቃጠለ።

[8] ሁለተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፥
የሚቃጠል ትልቅ ተራራ የሚመስል ነገር ወደ
ባሕር ተጣለ፥ የባሕር ሢሶ ደም ሆነ፥ [9] በባ
ሕር ውስጥ ከሚኖሩት ሕይወት ካላቸው ፍጥረ
ቶች ሢሶው ሞተ፥ የመርከቦች ሢሶ ወደመ።

[10] ሦስተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፥
እንደ ችቦ የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ ከሰማይ
ወደቀ፥ የወደቀውም በወንዞች ሢሶና በውሃ
ምንጮች ላይ ነው። [11] የኮከቡም ስም ፊቶ ይባ
ላል፥ የውሃው አንድ ሦስተኛ መራራ ሆነ፥
መራራ በሆነው ውሃ ጠንቅ ብዙ ሰዎች ሞቱ።

[12] አራተኛው መልአክ መለከቱን ነፋ፥ የፀ
ሐይ አንድ ሦስተኛ፥ የጨረቃ አንድ ሦስተኛ፥
የከዋክብት አንድ ሦስተኛ ተመታ፥ ስለዚህ የእነ
ርሱ አንድ ሦስተኛቸው ጨለመ፥ በዚህ ዐይነት
የቀን አንድ ሦስተኛና የሌሊት አንድ ሦስተኛ
ያለ ብርሃን ሆነ።

[13] ከዚህ በኋላ አንድ ንስር በሰማይ መካከል
ሲብርር አየሁ፥ በታላቅ ድምፅም እየጮኸ "የቀ
ሩት ሦስቱ መላእክት መለከት ሊነፉ ስለሚመ
ጣው የመለከት ድምፅ በምድር ላይ ለሚኖሩ
ሰዎች ወዮላቸው! ወዮላቸው! ወዮላቸው!"
ሲል ሰማሁ።

ምዕራፍ 9

[1] አምስተኛው መልአክ መለከቱን ነፋ፥
እነሆ ከሰማይ ወደ ምድር የወደቀ አንድ ኮከብ
አየሁ፥ የጥልቁ ጉድጓድ መክፈቻ ተሰጠው።
[2] እርሱ ጉድጓዱን ከፈተው፥ ጢስም ከታላቅ
ምድጃ እንደሚወጣ ጢስ ሆኖ ከጉድጓዱ
ወጣ፥ ከጉድጓዱ በወጣው ጢስ ምክንያት ፀሐ
ይና አየር ጨለሙ፥ [3] ከጢሱም ውስጥ አንበጣ
ዎች በምድር ላይ ወጡ፥ የምድር ጊንጦችን
ኀይል የመሰለ ኀይል ተሰጣቸው፥ [4] የምድርን
ሣር ሆነ ማናቸውንም የለመለመ ነገር ወይም
ማናቸውንም ዛፍ እንዳይጐዱ ተነገራቸው፥
መጐዳት ያለባቸው ግን በግንባራቸው ላይ የእግ
ዚአብሔር ማኅተም የሌለባቸውን ሰዎች ብቻ
ነበር። [5] እነርሱንም ቢሆን እምስት ወር ሰማሁ
ቃየት እንጂ ለመግደል ኀይል አልተሰጣቸ
ውም፥ የደረሰባቸውም ሥቃይ ጊንጥ ሰውን
ሲነድፍ እንደሚሰማው ዐይነት ያለ ነው። [6] በእ
ነዚያ ቀኖች ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ፥ ነገር
ግን አያገኙትም፥ ለመሞትም ይመኛሉ፥ ነገር
ግን ሞት ከእነርሱ ይሸሻል።

[7] አንበጣዎቹ ለመርነት እንደ ተዘጋጁ ፈረ
ሶች ይመስሉ ነበር፥ በራሳቸው ላይ የወርቅ
አክሊል የመሰለ ነገር ነበር፥ ፊታቸውም የሰው
ፊት ይመስል ነበር፥ [8] የሴት ጠጕር የመሰለ
ጠጕር ነበራቸው፥ ጥርሳቸው የአንበሳ ጥርስ
ይመስል ነበር፥ [9] የብረት ጥሩር የሚመስል
ጥሩር ነበራቸው፥ የክንፎቻቸው ድምፅ ወደ
ጦርነት የሚሄዱ ብዙ ፈረሶችና ሠረገላዎች
የሚያሰሙትን ድምፅ ይመስል ነበር። [10] እንደ
ጊንጥ ጅራትና መንደፊያ ነበራቸው፥ ሰዎችን
አምስት ወር የሚጐዱበት ኀይል የነበራቸው
በጅራታቸው ነበር። [11] ንጉሥም ነበራቸው፥
እርሱ የጥልቁ ጉድጓድ መልአክ ነው፥ ስሙም
በዕብራይስጥ አብዶን፥ በግሪክ አፀልዮን ይባ
ላል፥ ትርጕሙም ደምሳሽ ማለት ነው።

[12] የመጀመሪያው ወዮ አልፎአል፥ እነሆ
ከዚህ በኋላ ሌላ ሁለት ወዮ ገና ይመጣል።

[13] ስድስተኛው መልአክ መለከቱን ነፋ፥
እነሆ በእግዚአብሔር ፊት ካለው በወርቅ ከተ
ሠራው መሠዊያ የአራት ቀንዶች ድምፅ ሲወጣ
ሰማሁ። [14] መለከት የያዘውን ስድስተኛውን
መልአክ፥

"በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ የታሠሩትን አራ
ቱን መላእክት ፍታቸው!" አለው። [15] ለዚህ
ሰዓትና ለዚህ ቀን፥ ለዚህ ወርና ለዚህ ዓመት
የተዘጋጁት አራቱ መላእክት የሰዎችን አንድ

8:3 ፡- ኤሞጵ 9:1 ፡ ዘጽ. 30:1-3 ። 8:5 ፡- ዘሌ. 16:12 ፡ ሕዝ. 10:2 ፡ ዘጽ. 19:16 ፡ ራእ. 11:19 ፡ 16:18 ።
8:7 ፡- ዘጽ. 9:23-25 ፡ ሕዝ. 38:22 ። 8:10 ፡- ኢሳ. 14:12 ። 8:11 ፡- ኤር. 9:15 ። 8:12 ፡- ኢሳ. 13:10 ፡
ሕዝ. 32:7 ፡ ኢዩ. 2:10-31 ፡ 3:15 ። 9:2 ፡- ዘፍ. 19:28 ። 9:3 ፡- ዘጽ. 10:12-15 ። 9:4 ፡- ሕዝ. 9:4 ።
9:6 ፡- ኢዮብ 3:21 ፡ ኤር. 8:3 ። 9:7 ፡- ኢዩ. 2:4 ። 9:8 ፡- ኢዩ. 1:16 ። 9:9 ፡- ኢዩ. 2:5 ። 9:13 ፡- ዘጽ. 30:1-3 ።

ሦስተኛ እንዲገድሉ ተፈቱ። [16] የፈረሰኞቹ
ወራዊት ብዛት ሁለት መቶ ሚሊዮን ነበር፥
ቍጥራቸውንም ሰማሁ። [17] ፈረሶቹንና በፈረሶቹ
ላይ የተቀመጡትን ሰዎች በራእይ ያየኋቸው
በዚህ ዐይነት ነበር፥ በደረታቸው ላይ የነበረው
ጥሩር እንደ እሳት ቀይ፥ እንደ ያዕንት ሰማ
ያዊ፥ እንደ ዳን ቢጫ ይመስል ነበር፥ የፈረ
ሶቹ ራስ የአንበሳ ራስ ይመስል ነበር፥ ከአፋ
ቸው እሳትና ጢስ ዲንም ይወጣ ነበር፥ [18] ከአ
ፋቸው ባወጡት እሳት፥ ጢስ፥ ዲን፥ በእነዚህ
በሦስቱ መቅሠፍቶች የሰዎች አንድ ሦስተኛ
ተገደለ። [19] የፈረሶቹ ኀይል በአፋቸውና በጅራ
ታቸው ነበር፥ ጅራታቸው እባብ ይመስላል፥
የእባብ ራስም አለው፥ ሰውን የሚጐዱትም በእ
ርሱ ነበር።

[20] በእነዚህ መቅሠፍቶች ከመሞት የቀሩት
ሰዎች ከእጃቸው ሥራ ተመልሰው ንስሓ አልገ
ቡም፥ ምክንያቱም አጋንንትንና ከወርቅ፥
ከብር፥ ከናስ፥ ከድንጋይ፥ ከእንጨት የተሠሩ
ማየት ወይም መስማት ወይም መሄድ የማይች
ሉትን ጣዖቶች ማምለክ አልተዉም። [21] እንዲ
ሁም ከነፍሰገዳይነታቸው፥ ከሚርታቸው፥ ከሴ
ሰኛነታቸው፥ ከሌብነታቸውም ንስሓ አልገ
ቡም።

ምዕራፍ 10

መልአኩና ትንሹ መጽሐፍ

[1] ከዚህ በኋላ ደመና የለበሰ ሌላ ብርቱ መል
አክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ በራሱ ዙሪያ
ቀስተ ደመና ነበረ፥ ፊቱ እንደ ፀሐይ፥ እግሮቹ
እንደ እሳት ዐምዶች ነበሩ፥ [2] የተከፈተች
ትንሽ መጽሐፍ በእጁ ይዞ ነበር፥ ቀኝ እግሩን
በባሕር ላይ፥ ግራ እግሩንም በምድር ላይ
አኖረ፥ [3] የአንበሳ ድምፅ በመሰለ ታላቅ ድምፅ
ጮኸ፥ በጮኸም ጊዜ ሰባቱ ነጐድጓዶች በየድ
ምፃቸው ተናገሩ፥ [4] ሰባቱ ነጐድጓዶች በየድም
ፃቸው በተናገሩ ጊዜ እኔ ልጽፍ አሰብሁ፥ ነገር
ግን "ሰባቱ ነጐድጓዶች የተናገሩትን አሽገህ
በምስጢር ያዘው እንጂ አትጻፈው" የሚል
ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ።

[5] ከዚህ በኋላ በባሕርና በምድር ላይ ቆሞ
ያየሁት መልአክ ቀኝ እጁን ወደ ሰማይ አነ
ሣና፥ [6] ዘላለም በሚኖረው ሰማይንና በእርሱ
ያሉትን፥ ምድርንና በእርስዋም ያሉትን፥ ባሕ
ርንና በእርሱም ያሉትን በፈጠረው አምላክ
ስም ማለ፥ እንዲህም አለ፥ "ከእንግዲህ ወዲህ
አይዘገይም! [7] ነገር ግን ሰባተኛው መልአክ
መለከቱን በሚያሰማባቸው ቀኖች ለአገልጋዮቹ
ለነቢያት ባስታወቃቸው መሠረት የእግዚአብ
ሔር ምስጢር ይፈጸማል።" [8] ከሰማይ የሰማ
ሁት ድምፅ "በባሕርና በምድር ላይ የቆመው
መልአክ በእጁ የያዛትን የተፈታችውን መጽ
ሐፍ ሂድና ውሰድ" ሲል እንደገና ተናገረኝ።

[9] ወደ መልአኩም ሄጄ "ትንሹቱን መጽሐፍ
ስጠኝ" አልሁት፥ እርሱም "ውሰድና ብላት፥
በሆድህ መራራ ትሆናለች፥ በአፍህ ግን እንደ
ማር ትጣፍጣለች" አለኝ።

[10] እኔም ትንሹቱን መጽሐፍ ከመልአኩ እጅ
ወስጄ በላኋት፥ በአፌ እንደ ማር ጣፈጠች፥
ከበላኋት በኋላ ግን ሆዴ መራራ ሆነ። [11] ከዚህ
በኋላ "ስለ ብዙ ወገኖች፥ ሕዝቦች ልዩ ልዩ
ቋንቋ ስለሚናገሩ ሰዎችና ስለ ነገሥታት እንደ
ገና ትንቢት መናገር አለብህ" ተብሎ ተነገ
ረኝ።

ምዕራፍ 11

ሁለቱ ምስክሮች

[1] ከዚህ በኋላ ለመለኪያ የሚያገለግል አንድ
ረዥም ሸንበቆ ተሰጠኝ፥ እንዲህም ተባልሁ፥
"ተነሥ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና
መሠዊያውን ለካ፥ በዚያ የሚያመልኩትንም
ቍጠር፥ [2] ከቤተ መቅደሱ ውጪ ያለውን
ክፍት ቦታ ግን ተወው፥ እርሱ ለአረማውያን
የተሰጠ ስለሆነ አትለካው፥ አረማውያን ቅድስ
ቲቱን ከተማ አርባ ሁለት ወር ይረግጡአታል፥
[3] ሁለቱ ምስክሮቼ የሐዘን ልብስ ለብሰው አንድ
ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ቀን ትንቢት እንዲናገሩ
ኀይል እሰጣቸዋለሁ።"

[4] እነርሱ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ
የወይራ ዛፎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው፥
[5] ማንም እነርሱን ሊጐዳ ቢፈልግ እሳት ከአፋ
ቸው ወጥቶ ጠላቶቻቸውን ያቃጥላል፥ እነር
ሱን ሊጐዳ የሚፈልግ ሁሉ የሚሞተው በዚህ
ዐይነት ነው። [6] እነርሱ ትንቢት በሚናገሩባ
ቸው በእነዚህ ቀኖች ዝናም እንዳይዘንም ሰማ
ይን ለመዝጋት ሥልጣን አላቸው፥ እንዲሁም
ውሃዎችን ወደ ደም ለመለወጥና በሚፈልጉ
ትም ጊዜ ሁሉ በማንኛውም ዐይነት መቅሠ
ፍት ምድርን ለመምታት ሥልጣን አላቸው።

[7] ምስክርነታቸውን ከጨረሱ በኋላ ከጥልቁ
ጉድጓድ የሚወጣው አውሬ ከእነርሱ ጋር ተዋ
ግቶ ያሸንፋቸዋል፥ ይገድላቸዋልም፥ [8] ሬሳቸ
ውም በምሳሌያዊ አጠራር ሰዶም ወይም ግብጽ
በምትባል በታላቂቱ ከተማ አደባባይ ይጋደ
ማል፥ ይህች ከተማ የእነርሱ ጌታ የተሰቀለባት
ናት። [9] ከልዩ ልዩ ወገንና ነገድ፥ ከልዩ ልዩ

9:20 ፡- መዝ. 115:4-7 ፡ 135:15-17 ፡ ዳን. 5:23 ። 10:5-7 ፡- ዘጽ. 20:11 ፡ ዘዳ. 32:40 ፡ ዳን. 12:7 ፡ ኦሞጵ 3:7 ።
10:8-10 ፡- ሕዝ. 2:8-33 ። 11:1 ፡- ሕዝ. 40:3 ፡ ዘካ. 2:1-2 ። 11:2 ፡- ሉቃ. 21:24 ። 11:4 ፡- ዘካ. 4:3 ፡ 11-14 ።
11:6 ፡- 1ነገ. 17:1 ፡ ዘጽ. 7:17-19 ፡ 1ሳሙ. 4:8 ። 11:7 ፡- ዳን. 7:7 ፡ 21 ፡ ራእ. 13:5-7 ፡ 17:8 ።
11:8 ፡- ኢሳ. 1:9-10 ።

ቋንቋና ሕዝብ የሆኑ ሰዎች ሦስት ቀን ተኩል
ሬሳቸውን ይመለከታሉ ፤ ሬሳቸው እንዳይቀ-
ርም ይከለክላሉ ፤ 10 እነዚህ ሁለቱ ነቢያት የም-
ድር ሰዎችን ስላስጨነቁ ፥ በምድር የሚኖሩ
ሰዎች በነቢያቱ ሞት ደስ ይላቸዋል ፤ በደስ
ታም በዓል ያደርጋሉ ፤ ስጦታም ይለዋወጣሉ ፤
11 ነገር ግን ሦስት ቀን ተኩል ካለፈ በኋላ ሕይ-
ወት የሚሰጥ እስትንፋስ ከእግዚአብሔር መጥቶ
ወደ ሬሳዎቹ ገባ ፤ በእግራቸውም ቆሙ ፤ ያዩአ-
ቸውም ሰዎች እጅግ ፈሩ ። 12 ከዚህ በኋላ
ሁለቱ ነቢያት "ወደዚህ ውጡ!" የሚል ታላቅ
ድምፅ ከሰማይ ሰሙ ፤ ጠላቶቻቸው እየተመለከ-
ቱአቸውም በደመና ወደ ሰማይ ወጡ ። 13 በዚ-
ያኑ ሰዓት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ ፤ የከተ-
ማይቱም አንድ ዐሥረኛ ወደመ ፤ በምድር መና-
ወጥም ምክንያት ሰባት ሺ ሰዎች ሞቱ ፤ ከሞት
የተረፉትም እጅግ ፈሩ ፤ የሰማይንም አምላክ
አከበሩ ።

14 ሁለተኛው ወዮ አለፈ ፤ እነሆ ሦስተኛው
ወዮ ቶሎ ይመጣል ።

ሰባተኛው መለከት

15 ሰባተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ ፤ በሰ-
ማይም "የዓለም መንግሥት የጌታ የአምላካች-
ንና የመሲሑ ሆናለች ፤ እርሱ ለዘላለም ይነግ-
ሣል!" የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ተሰሙ ።
16 በእግዚአብሔር ፊት በዙፋኖቻቸው ላይ የተ-
ቀመጡት ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችም በግምባራ-
ቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ ፤ 17 እን-
ዲህም አሉ ፥

"ያለህና የነበርህ ፤
ሁሉን የምትችል ጌታ እግዚአብሔር
ሆይ!
ትልቁን ሥልጣንህን በእጅህ
ስላደረግህና
ስለ ነገሥህ እናመሰግንሃለን ።
18 አረማውያን ሕዝቦች ተቆጡ ፤
የአንተም ቍጣ መጣ ፤
በሙታን ላይ የምትፈርድበት ጊዜም
ደረሰ ፤
ለአገልጋዮችህ ለነቢያትና
ለቅዱሳን ስምህንም ለሚያከብሩት ፥
ለታናናሾችና ለታላላቆች ፥
ሽልማታቸውን የምትሰጥበት ጊዜ ደረሰ ፤
ምድርን ያጠፉአትን የምታጠፋበት
ጊዜም ደረሰ ።"

19 በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር ቤተ መቅ-
ደስም ተከፈተ ፤ የእርሱም የኪዳን ታቦት በቤተ
መቅደሱ ውስጥ ታየ ። መብረቅ ፥ ድምፅ ፥
ነጐድጓድ ፥ የምድር መናወጥና ታላቅም በረዶ
ሆነ ።

ምዕራፍ 12

ሴቲቱና ዘንዶው

1 ከዚህ በኋላ ታላቅና አስደናቂ ምልክት በሰ-
ማይ ታየ ፤ ፀሐይን የለበሰች ፥ ጨረቃን ከእግሯ
በታች ያደረገች ፥ ዐሥራ ሁለት ኮከቦችን እንደ
አክሊል በራስዋ ላይ የደፋች አንዲት ሴት
ታየች ። 2 እርሰዋም ነፍሰ ጡር ነበረች ፤ ምጥ
ይዞአትም ተጨንቃ ትጮኽ ነበር ፤

3 እንዲሁም ሌላ ምልክት በሰማይ ታየ ፤
ሰባት ራሶችና ዐሥር ቀንዶች የነበሩት ትልቅ
ቀይ ዘንዶ ታየ ፤ በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች
ደፍቶ ነበር ፤ 4 በጅራቱ የኮከቦችን አንድ ሦስ-
ተኛ ከሰማይ ስቦ ወደ ምድር ጣላቸው ፤ ሴቲቱ
በምትወልድበት ጊዜ ልጅዋን ለመዋጥ አሰቦ
ዘንዶው ልትወልድ ወደተቃረበችው ሴት ሄደና
ከፊት ለፊትዋ ቆመ ፤ 5 ሴቲቱም ሕዝቦችን
ሁሉ በብረት በትር የሚገዛ ወንድ ልጅ ወለ-
ደች ፤ ልጅዋ ግን ወደ እግዚአብሔርና ወደ
ዙፋኑ ተወሰደ ፤ 6 ሴቲቱም ወደ በረሓ ሸሽታ
ሄደች ፤ እዚያ አንድ ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ቀን
በክብካቤ ተይዛ የምትጠበቅበትን ስፍራ እግዚአ-
ብሔር አዘጋጅቶላት ነበር ።

7 በሰማይ ጦርነት ተነሣ ፤ ሚካኤልና የእርሱ
መላእክት ከዘንዶውና ከመላእክቱ ጋር ተዋጉ ፤
8 ነገር ግን ዘንዶውና መላእክቱ ተሸነፉ ፤ ከዚ-
ያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም ።
9 ታላቁም ዘንዶ ወደታች ተጣለ ፤ እርሱ ሰዎ-
ችን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስ ወይም ሰይ-
ጣን ተብሎ የሚጠራው የቀድሞው እባብ
ነው ። እርሱ ወደ ምድር ተጣለ ፤ የእርሱም
መላእክት ከእርሱ ጋር አብረው ተጣሉ ።

10 ከዚህ በኋላ አንድ ታላቅ ድምፅ በሰማይ
እንዲህ ሲል ሰማሁ ፥ "እነሆ ማዳንና ኀይል
መንግሥትም የአምላካችን ሆኖአል! ሥልጣንም
የመሲሑ ሆኖአል! ምክንያቱም ወንድሞቻችንን
በአምላካችን ፊት ቀንና ሌሊት ሲያሰጣቸው የነ-
በረ የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአል ፤ 11 እነርሱ
በበጉ ደምና በተናገሩት የምስክርነት ቃል ድል
ነሥተውታል ፤ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ራሳቸ-
ውን ለሞት አሳልፈው ሰጥተዋል ፤ 12 ስለዚህ
ሰማይና በውስጣቸው የምትኖሩ ሁሉ ደስ ይበላ-
ችሁ! ምድርና ባሕር ግን ወዮላችሁ! ምክንያ-
ቱም ጥቂት ጊዜ እንደ ቀረው ስላወቀ ዲያብሎስ
በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአል ።"

11:11 ፡- ሕዝ. 37:10 ። 11:12 ፡- 2ነገ. 2:11 ። 11:13 ፡- ሩት. 6:12 ፡ 16:18 ። 11:15 ፡- ዘጸ. 15:18 ፡ ዳን. 2:44 ፡ 7:14 ፡27 ። 11:18 ፡- መዝ. 2:5 ፡ 110:5 ፡ 115:13 ። 11:19 ፡- ሩት. 8:5 ፡ 16:18 ፡21 ። 12:3 ፡- ዳን. 7:7 ። 12:4 ፡- ዳን. 8:10 ። 12:5 ፡- ኢሳ. 66:7 ፡ መዝ. 2:9 ። 12:7 ፡- ዳን. 10:13 ፡21 ፡ 12:1 ፡ ይሁ.9 ። 12:9 ፡- ዘፍ. 3:1 ፡ ሉቃ. 10:18 ። 12:10 ፡- ኢዮብ 1:9-11 ፡ ዘካ. 3:1 ።

13 ዘንዶው ወደ ምድር እንደተጣለ ባየ
ጊዜ ፥ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደ-
ዳት ፤ 14 ሴቲቱ በበረሓ ወደ ተዘጋጀላት ስፍራ
በርራ እንድትሄድ የታላቅ ንስር ክንፎች የሚመ-
ስሉ ሁለት ክንፎች ተሰጡአት ፤ እዚያም ከእ-
ባቡ ፊት ርቃ ሦስት ዓመት ተኩል በክብካቤ
ተይዛ ትጠበቅ ነበር ። 15 ሴቲቱ በጕርፍ እንድ-
ትወሰድ ብሎ እባቡ የወንዝ ውሃ የሚያህል
ውሃ ከአፉ ተፍቶ በስተኋላዋ አፈሰሰ ። 16 ነገር
ግን ምድር ሴቲቱን ረዳቻት ፤ አፍዋንም ከፈተ-
ችና ዘንዶው ከአፉ ተፍቶ ያፈሰሰውን ውሃ
ዋጠች ። 17 ዘንዶው በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ ከእር-
ስዋ ዘር ተርፈው ከቀሩት ጋር ሊዋጋ ሄደ ። እነ-
ርሱም የእግዚአብሔርን ትእዛዞች የሚጠብቁና
ለኢየሱስ በታማኝነት የሚመሰክሩ ናቸው ።
18 ዘንዶውም በባሕሩ ዳር ፥ አሸዋ ላይ ቆመ ።

ምዕራፍ 13

ሁለቱ አውሬዎች

1 ከዚህ በኋላ አንድ አውሬ ከባሕር ሲወጣ
አየሁ ፤ ዐሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት ፤
በቀንዶቹም ላይ ዐሥር ዘውዶች ነበሩ ፤ በራሶ-
ቹም ላይ የስድብ ስሞች ነበሩ ። 2 ያየሁት
አውሬ ነብር ይመስል ነበር ፤ እግሮቹ የድብ
እግሮች ፥ አፉ የአንበሳ አፍ ይመስል ነበር ።
ዘንዶው የራሱን ኀይልና የራሱን ዙፋን ትል-
ቅም ሥልጣን ለአውሬው ሰጠው ። 3 ከራሶቹ
አንዱ ለሞት የሚያደርስ ቍስል እንደነበረው
ሆኖ አየሁት ፤ ነገር ግን ለሞት የሚያደርሰው
ቍስሉ ድኖአል ፤ ዓለም በሙሉ በመደነቅ አው-
ሬውን ተከተለ ። 4 ለአውሬው ሥልጣን በመስ-
ጠቱ ሰዎች ሁሉ ለዘንዶው ሰገዱለት ፤ "አውሬ
ውን የሚመስል ማን ነው? ከእርሱስ ጋር ማን
ሊዋጋ ይችላል?" እያሉ ፥ ለእርሱም ሰገዱ-
ለት ።

5 የትዕቢትና የስድብ ቃል የሚናገርበት አፍ
ለአውሬው ተሰጠው ፤ አርባ ሁለት ወር በሥል-
ጣን እንዲሠራም ተፈቀደለት ። 6 እግዚአብሔር
ንና የእግዚአብሔርን ስም ፥ መኖሪያውንና በሰ-
ማይ የሚኖሩትን መላእክት ጀመረ ። 7 ቅዱሳንን
እንዲዋጋና ድል እንዲነሳቸው ሥልጣን ተሰ-
ጠው ፤ በነገድና በወገን ፥ በቋንቋና በሕዝብ
ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው ። 8 ዓለም ሲፈጠር
ጀምሮ ስሞቻቸው በታረደው በግ የሕይወት
መጽሐፍ ያልተጻፈ በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች
ሁሉ ለአውሬው ይሰግዳሉ ።

9 ሰሚ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ! 10 "ለመማ-
ረክ የተመደበ ይማረካል ፤ በሰይፍ ለመገደል
የተመደበ በሰይፍ ይገደላል ፤" እንግዲህ የቅዱ-
ሳን ትዕግሥትና እምነት የሚታየው በዚህ ጊዜ
ነው ።

11 ሌላ አውሬ ደግሞ ከምድር ሲወጣ
አየሁ ፤ የበግ ቀንዶች የሚመስሉ ሁለት ቀን-
ዶች ነበሩት ፤ አነጋገሩም እንደ ዘንዶው ነበር ፤
12 የመጀመሪያውን አውሬ ሥልጣን ሁሉ ፥
በመጀመሪያው አውሬ ፊት ሆኖ ይሠራበት
ነበር ፤ ምድርና በእርስዋ ላይ የሚኖሩት ሁሉ
ለአውሬው እንዲሰግዱለት ያደርጋል ፤ ይህም
አውሬ ያ ለሞት የሚያደርስ ቍስል የዳነለት
የመጀመሪያው አውሬ ነው ። 13 ይህ ሁለተኛው
አውሬ በሰዎች ፊት እሳትን ከሰማይ እስከማው-
ረድ ድረስ ባለው ሥልጣን ታላላቅ ተአምራትን
ያደርግ ነበር ። 14 በመጀመሪያው አውሬ ፊት
እንዲያደርግ በተፈቀደለት ተአምራት ምክንያት
በምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ያስት ነበር ፤
በሰይፍ ቈስሎ የዳነውን የአውሬውን ምስል እን-
ዲሠሩም በምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ያዝዛ-
ቸዋል ። 15 ሁለተኛው አውሬ ለመጀመሪያው
አውሬ ምስል የሕይወት እስትንፋስ ለመስጠት
ሥልጣን ተሰጠው ፤ የሕይወት እስትንፋስ ለመ-
ስጠት ሥልጣን የተሰጠውም ምስሉ ለመናገር
እንዲችልና ለእርሱ የማይሰግዱት ሁሉ እንዲገ-
ደሉ ያደርግ ዘንድ ነው ። 16 ሁለተኛው አውሬ
ታናናሾችም ሆኑ ታላላቆች ፥ ሀብታሞችም ሆኑ
ድኾች ፥ ጌቶችም ሆኑ አገልጋዮች ሁሉም
በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ላይ ምል-
ክት እንዲያደርጉ አስገደዳቸው ። 17 በዚህ ወይ-
ነት የአውሬው ስም የሆነው ምልክት ወይም
የስሙ ቍጥር የሌለው ማንም ሰው መግዛትም
ሆነ መሸጥ አይችልም ።

18 ጥበብ ያለው እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ፤
አእምሮ ያለው የአውሬውን ቍጥር ያስላው ፤
ቍጥሩ የሚያመለክተው ሰውን ነው ፤ ቍጥሩም
ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ነው ።

ምዕራፍ 14

በጉና መቶ አርባ አራቱ ሺ ሰዎች

1 ከዚህ በኋላ እነሆ በጉ በጽዮን ተራራ ላይ
ቆሞ አየሁ ፤ ከእርሱ ጋር የእርሱ ስምና የአባቱ
ስም በግንባራቸው ላይ የተጻፈባቸው መቶ
አርባ አራት ሺ ሰዎች ነበሩ ። 2 ከሰማይም የታ-
ላቅ ፏፏቴ ውሃ ድምፅና የታላቅ ነጐድጓደ-
የመሰለ ድምፅ ሰማሁ ፤ የሰማሁትም ድምፅ
በገና ደርዳሪዎች በገና እየደረደሩ የሚያሰሙ-
ትን ድምፅ ይመስል ነበር ። 3 በዙፋኑና በአራቱ
እንስሶች በሽማግሌዎችም ፊት መቶ አር-
አራቱ ሺ ሰዎች አዲስ መዝሙር ዘመሩ ፤ ይህ-
መዝሙር ከምድር ከተዋጁት ከመቶ አር-

12:14 ፡- ዳን. 7:25 ፡ 12:7 ። 13:1 ፡- ዳን. 7:3 ፡ ሩት. 17:3 ፡7-12 ። 13:2 ፡- ዳን. 7:4-6 ። 13:5-6 ፡- ዳን. 7:8 ፡25 ፡ 11:36 ። 13:7 ፡- ዳን. 7:21 ። 13:8 ፡- መዝ. 69:28 ። 13:10 ፡- ኤር. 15:2 ፡ 43:11 ። 14:1 ፡- ሕዝ. 9:4 ፡ ሩት. 7:3 ።

አራቱ ሺ ሰዎች በቀር ማንም ሊማረው አልቻ
ለም ። [4]እነርሱ ድንግሎች ስለሆኑ ከሴቶች ጋር
በግብረ ሥጋ በመነናኘት ያልረከሱ ናቸው ፤ እነ
ርሱ በጉ ወደሚሄድበት ሁሉ የሚከተሉት
ናቸው ፤ እነርሱ ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኩ
ራት ለመሆን ከሰዎች መካከል የተዋጁ
ናቸው ፤ [5]እነርሱ ሐሰት ተናግረው አያው
ቁም ፤ ነቀፋም የሌለባቸው ናቸው ።

የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚያስታውቁ
ሦስቱ መላእክት

[6]ከዚህ በኋላ በምድር ላይ ለሚኖሩ ለሕዝ
ብና ለነገድ ለቋንቋና ለወገን ሁሉ ለማብሠር
ዘላለማዊውን የምሥራች ቃል የያዘ ሌላ መል
አክ በሰማይ መካከል ሲበርር አየሁ ። [7]በታላቅ
ድምፅም "እግዚአብሔርን ፍሩ ፤ አክብሩትም ፤
ምክንያቱም የእርሱ የፍርድ ሰዓት ደርሶአል ፤
ሰማይንና ምድርን ባሕርንና የውሃ ምንጮችን
ለፈጠረ አምላክ ስገዱ!" አለ ።

[8]ሌላም ሁለተኛው መልአክ "የዝሙትዋ
ፍትወት የሆነውን የሚያሰክር የወይን ጠጅ
ለሕዝቦች ሁሉ ያጠጣች ፥ ታላቂቱ ባቢሎን
ወደቀች! ወደቀች!" እያለ የመጀመሪያውን
መልአክ ተከተለ ።

[9]ሌላ ሦስተኛ መልአክም በታላቅ ድምፅ
እንዲህ እያለ ተከተላቸው ፤ "ለአውሬውና ለም
ስሉ የሚሰግዱ ፥ ምልክቱን በግምባራቸው
ወይም በእጃቸው የሚያደርጉ ሁሉ ፤ [10]የእግዚ
አብሔርን የቁጣ የወይን ጠጅ ይጠጣሉ ፤
ይህም የወይን ጠጅ ሳይበረዝ በቍጣው ጽዋ
የተዘጋጀ ነው ፤ እንዲሁም በቅዱሳን መላእክት
ፊትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሠቃያሉ ፤
[11]እነርሱን ከሚሠቃየው እሳት የሚወጣው
ጢስ ለዘላለም ወደ ላይ ይወጣል ፤ ለአውሬውና
ለምስሉ የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት ያደረጉ
ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም ።"

[12]የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጠብቁና
አያሱስንም በማመን የሚጸኑ ቅዱሳን ፤ ትዕግሥ
ታቸው የሚታየው እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ።

[13]ከሰማይም እንዲህ የሚል ድምፅ ሰማሁ ፥
ይህንን ጻፍ ፤ "ከእንግዲህ ወዲህ የጌታ ኢየሱስ
ሆነው የሚሞቱ ዕድለኞች ናቸው ፤" መንፈስ
ቅዱስም "አዎ! ከድካማቸው እንዲያርፉ ሥራ
ቸው ይከተላቸዋል" ይላል ።

የመከር ጊዜ

[14]ከዚህ በኋላ እነሆ ነጭ ደመና አየሁ ፤
በደመናው ላይ የሰውን ልጅ የሚመስል ተቀም
ጦአል ፤ በራሱ ላይ የወርቅ አክሊል አድርጎ
አል ፤ በእጁ ስለታም ማጭድ ይዞአል ፤ [15]ሌላ
መልአክ ከመቅደሱ ወጣና በደመና ላይ የተቀ
መጠውን በታላቅ ድምፅ "የምድር መከር ደርሶ
አል! የዐጨዳ ሰዓትም ቀርቦአል! ስለዚህ ማጭ
ድህን ስደድና ዕጨድ" አለ ። [16]በደመናው ላይ
የተቀመጠውም ማጭዱን ወደ ምድር ሰደ
ደው ፤ ምድርም ታጨደች ።

[17]ሌላ መልአክም በሰማይ ካለው መቅደስ
ወጣ ፥ እርሱም ስለታም ማጭድ ይዞ ነበር ።

[18]በእሳት ላይ ሥልጣን ያለው ሌላ መልአክ
ከመሠዊያው አጠገብ ወጣና ስለታም ማጭድ
የያዘውን መልአክ "የዘለላዎቹ ፍሬዎች ስለበ
ሰሉ የወይን ዘለላዎችን ሁሉ ከምድር ወይን
ቍረጥ!" በማለት በታላቅ ድምፅ ጮኸ ።
[19]መልአኩም ማጭዱን ወደ ምድር ሰደደው ፤
የምድርንም ወይን ዘለላ ቈረጠ ፤ የእግዚአብሔ
ርን ቍጣ በሚያመለክት ታላቅ መጭመቂያ
ውስጥ ጣለው ። [20]ከከተማው ውጭ ባለው በወ
ይን መጭመቂያም ተጨመቀ ፤ ከመጭመቂያ
ውም እስከፈረስ ልጓም ወደ ላይ ከፍ ያለና
ሦስት መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት የሚደርስ ደም
ወጥቶ ፈሰሰ ።

ምዕራፍ 15

የመጨረሻዎቹን መቅሠፍቶች የያዙ መላእክት

[1]ሌላም ታላቅና ድንቅ ምልክት በሰማይ
አየሁ ፤ የእግዚአብሔር ቍጣ የሚፈጸምባቸውን
የመጨረሻ የሆኑትን ሰባት መቅሠፍቶች የያዙ
ትን ሰባት መላእክት አየሁ ።

[2]ከዚህ በኋላ እሳት የተቀላቀለበት የሚመ
ስል የመስተዋት ባሕር አየሁ ፤ አውሬውንና
የአውሬውን ምስል የስሙንም ቍጥር ድል የነ
ሡትን አየሁ ፤ እግዚአብሔር የሰጣቸውን በገና
ይዘው በመስተዋቱ ባሕር አጠገብ ቆመው
ነበር ። [3]የእግዚአብሔርን አገልጋይ የሙሴን
መዝሙርና የበጉን መዝሙር እንዲህ እያሉ ይዘ
ምሩ ነበር ፥

"ሁሉን የምትችል ጌታ አምላክ ሆይ!
ሥራህ ታላቅና አስደናቂ ነው ፤
የሕዝቦች ንጉሥ ሆይ!
መንገድህ ትክክልና እውነት ነው ፤
[4] ጌታ ሆይ! አንተን የማይፈራና
ስምህንም የማያከብር ማን ነው?
ምክንያቱም ቅዱስ አንተ ብቻ ነህ ፤
የእውነት ፍርድህ ስለተገለጠ ፥
ሕዝቦች ሁሉ መጥተው በፊትህ
ይሰግዳሉ ።"

[5]ከዚህም በኋላ እንደገና አየሁ ፤ እነሆ የም
ስክር ድንኳን የሆነው ቤተ መቅደስ በሰማይ

14:5 ፡- ዘኁ. 3:13 ። 14:8 ፡- ኢሳ. 21:9 ፡ ኤር. 51:8 ፡ ራእ. 18:2 ። 14:10 ፡- ኢሳ. 51:17 ፡ ዘፍ. 19:24 ፡ ሕዝ. 38:22 ። 14:11 ፡- ኢሳ. 34:10 ። 14:14 ፡- ዳን. 7:13 ። 14:15 ፡- ኢዩ. 3:13 ። 14:20 ፡- ኢሳ. 63:3 ፡ ሰቆ. 1:15 ፡ ራእ. 19:15 ። 15:3 ፡- ዘጽ. 15:1 ። 15:4 ፡- ኤር. 10:7 ፡ መዝ. 86:9 ። 15:5 ፡- ዘጽ. 38:21 ።

ተከፈተ ፤ [6]ሰባቱን መቅሠፍቶች የያዙት ሰባቱ
መላእክት ከቤተ መቅደሱ ወጡ ፤ የሚያንጸባ
ርቅ ነጭ ልብስ ለብሰው ነበር ፤ ደረታቸውንም
በወርቅ መታጠቂያ ታጥቀው ነበር ። [7]ከአራቱ
እንስሶች አንዱ በዘላለማዊው አምላክ ቍጣ የተ
ሞሉትን ሰባት የወርቅ ጽዋዎች ለሰባቱ መላእ
ክት ሰጣቸው ፤ [8]ቤተ መቅደሱም ከእግዚአብ
ሔር ክብርና ኀይል የተነሣ በጢስ ተሞላ ፤
ሰባቱ መላእክት የያዙአቸው ሰባት መቅሠፍ
ቶች እስከተፈጸሙ ድረስ ፥ ማንም ወደ ቤተ
መቅደሱ መግባት አልቻለም ።

ምዕራፍ 16

የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች

[1]ከዚህ በኋላ ሰባቱን መላእክት "ሂዱ! ሰባ
ቱን የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች በምድር
ላይ አፍስሱ!" የሚል ታላቅ ድምፅ ከቤተ
መቅደስ ሲወጣ ሰማሁ ።

[2]የመጀመሪያው መልአክ ሄደና ጽዋውን
በምድር ላይ አፈሰሰ ፤ የአውሬው ምልክት ባለ
ባቸውና ለአውሬው ምስል በሚሰግዱ ሰዎች
ላይ መጥፎና የሚያሠቃይ ቍስል ወጣባቸው ።

[3]ሁለተኛው መልአክ ጽዋውን በባሕር ላይ
አፈሰሰ ፤ ባሕሩም እንደ ሞተ ሰው ደም ሆነ ፤
በባሕሩ ይኖሩ የነበሩት ሕይወት ያላቸው ነገ
ሮች ሁሉ ሞቱ ።

[4]ሦስተኛው መልአክ ጽዋውን በወንዞችና
በውሃ ምንጮች ላይ አፈሰሰ ፤ እነርሱም ደም
ሆኑ ፥ [5]በውሃ ላይ ሥልጣን ያለው መልአክ እን
ዲህ ሲል ሰማሁ ፥ "ያለህና የነበርህ ቅዱስ ጌታ
ሆይ! እንዲህ ስለ ፈረድህ እውነተኛ ነህ ፤
[6]ሰዎች የቅዱሳንንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ ፥
ደም አጠጣሃቸው ፤ ይህም የሚገባቸው ነው ፤"
[7]በመሠዊያውም "አዎ ፥ ሁሉን የምትችል
ጌታ አምላክ ሆይ! ፍርድህ እውነትና ትክክል
ነው" የሚል ድምፅ ሰማሁ ።

[8]አራተኛው መልአክ ጽዋውን በፀሐይ ላይ
አፈሰሰ ፤ ፀሐይም ሰዎችን በግለትዋ ለማቃጠል
ኀይል ተሰጣት ፤ [9]ሰዎች በታላቅ ግለት ተቃ
ጠሉ ፤ በእነዚህ መቅሠፍቶች ላይ ሥልጣን ያለ
ውን የእግዚአብሔርን ስም ተሳደቡ ፤ ንስሓ
መግባትና እርሱን ማክበር እምቢ አሉ ።

[10]አምስተኛው መልአክ ጽዋውን በአው
ሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ ፤ የአውሬውም መንግ
ሥት ጨለማ ሆነ ፤ ሰዎች ከሥቃያቸው የተነሣ
ምላሳቸውን ያኝኩ ነበር ፤ [11]ከሥቃያቸውና
ከቁስላቸው የተነሣ የሰማይን አምላክ ተራ
ገሙ ፤ ከሥራቸውም ንስሓ አልገቡም ።

[12]ስድስተኛው መልአክ ጽዋውን በታላቁ
ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ ፤ ከምሥራቅ
ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ ለማዘጋጀት የወ
ንዙ ውሃ ደረቀ ። [13]ከዘንዶው አፍና ከአውሬው
አፍ ፥ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጉንቸሮች
የሚመስሉ ሦስት ርኵሳን መናፍስት ሲወጡ
አየሁ ። [14]እነርሱ ተአምራት የሚያደርጉ የአጋ
ንንት መናፍስት ናቸው ፤ እነዚህ ሦስት መናፍ
ስት ሁሉን በሚችል አምላክ ታላቅ ቀን ለሚሆ
ነው ጦርነት ሰዎችን ለመሰብሰብ ወደ መላው
የዓለም ነገሥታት ሁሉ ይሄዳሉ ።

[15]"እነሆ እኔ እንደ ሌባ በድንገት እመጣ
ለሁ ፤ ራቁቴን እንዳይሆንና ሐፍረቴን ሰዎች
እንዳያዩበት ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ሰው የተ
መሰገነ ነው ።"

[16]መናፍስቱ ነገሥታቱን ሰብስበው በዕብራ
ይስጥ አርማጌዶን በሚባል ስፍራ ለጦርነት አስ
ከተቱአቸው ።

[17]ሰባተኛው መልአክ ጽዋውን በዐየር ላይ
አፈሰሰ ፤ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ካለው ዙፋን
"ተፈጸመ!" የሚል ታላቅ ድምፅ ወጣ ።
[18]መብረቅ ፥ ድምፅ ፥ ነጐድጓድና ታላቅ የም
ድር መናወጥ ሆነ ፤ ይህን የመሰለ ታላቅ የም
ድር መናወጥ ሰው በምድር ላይ ከተፈጠረ
ጀምሮ ሆኖ አያውቅም ። [19]ታላቂቱ ከተማ ከሦ
ስት ተከፈለች ፤ የሕዝቦች ከተሞችም ተደመ
ሰሱ ፤ እግዚአብሔር ታላቂቱን ባቢሎንን አስታ
ወሰ ፤ የብርቱ ቍጣው ወይን ጠጅ የተሞላበትን
ጽዋ እንድትጠጣ አደረጋት ። [20]ደሴቶች ሁሉ
ጠፉ ፤ ተራራዎችም በነበሩበት አልተገኙም ፤
[21]እያንዳንዱ አርባ ኪሎ ግራም ያህል የሚመ
ዝን በረዶ በሰዎች ላይ ከሰማይ ወረደባቸው ፤
መቅሠፍቱ እጅግ አሠቃቂ ስለነበረ ሰዎች በበረ
ዶው መቅሠፍት ምክንያት እግዚአብሔርን
ተራገሙ ።

ምዕራፍ 17

ታላቂቱ አመንዝራ ሴት

[1]ሰባቱን ጽዋዎች ይዘው ከነበሩት ከሰባቱ
መላእክት አንዱ ወደ እኔ መጥቶ እንዲህ
አለኝ ፥ "ና በብዙ ውሃዎች ላይ የተቀመጠች
ውን የታላቂቱን አመንዝራ ሴት የቅጣት ፍርድ
አሳይሃለሁ ፤ [2]የምድር ነገሥታት ከእርስዋ ጋር
አመንዝረዋል ፤ የምድር ነዋሪዎችም በዝሙትዋ
የወይን ጠጅ ሰክረዋል ።"

[3]ከዚህ በኋላ መልአኩ በመንፈስ ወደ በረሓ
ወሰደኝ ፤ በሁለተኛው የስድብ ስሞች ሙሉ
ቱ ፥ ሰባት ራሶችና ዐሥር ቀንዶች ባሉት

15:8 ፡- ዘጽ. 40:34 ፡ 1ነገ. 8:10-11 ፡ 2ዜ.መ.5:13-14 ፡ ኢሳ. 6:4 ። 16:2 ፡- ዘጽ. 9:10 ። 16:15 ፡- ማቴ. 24:43-44 ፡ ሉቃ. 12:39-40 ፡ ራእ. 3:3 ። 16:16 ፡- 2ነገ. 23:29 ፡ ዘካ. 12:11 ። 16:18 ፡- ራእ. 8:5 ፡ 11:13 ፡ 19 ። 16:19 ፡- ኢሳ. 51:17 ። 16:20 ፡- ራእ. 6:14 ። 16:21 ፡- ዘጽ. 9:23 ፡ ራእ. 11:19 ። 17:1 ፡- ኤር. 51:13 ። 17:2 ፡- ኢሳ. 23:17 ፡ ኤር. 51:7 ። 17:3 ፡- ራእ. 13:1 ።

በቀይ አውሬ ላይ የተቀመጠች አንዲት ሴት
አየሁ ። 4ሴቲቱ ሐምራዊና ቀይ ልብስ ለብሳ
ነበር ፤ በወርቅና በከበረ ድንጋይ በዕንቊዎችም
አሸብርቃ ነበር ፤ በእጅዋም የሚያስጸይፍ ነገ
ርና የዝሙትዋ ርኵሰት የሞላበትን የወርቅ ጽዋ
ይዛ ነበር ። 5በግምባርዋም ላይ “የአመንዝሮ
ችና የምድር ርኵሰቶች እናት ፥ ታላቂቱ ባቢ
ሎን” የሚል ምስጢራዊ ነገር ያለበት ስም
ተጽፎ ነበር ። 6ያቺ ሴት በቅዱሳን ደምና በኢ
የሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት ፤ ባየኋትም
ጊዜ እጅግ በጣም ተደነቅሁ ። 7መልአኩ ግን
እንዲህ አለኝ ፥ “ስለምን ትደነቃለህ? የሴቲቱን
ምስጢርና እርስዋ የተቀመጠችበትን ፥ ሰባት
ራሶችና ዐሥር ቀንዶች ያሉትን ፥ የአውሬውን
ምስጢር እገልጥልሃለሁ ፤ 8ያየኸው አውሬ
ቀድሞ ነበር ፤ አሁን የለም ፤ በኋላ ከጥልቁ
ጕድጓድ ይወጣል ፤ ወደ ጥፋቱም ይሄዳል ፤
ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ ስሞቻቸው በሕይወት
መጽሐፍ ያልተጻፉ የምድር ነዋሪዎች ፥ አው
ሬው ቀድሞ የነበረ ፥ አሁን የሌለ ፥ በኋላ የሚ
መጣ መሆኑን ሲያዩ ይደነቃሉ ።

9“ጥበብ ያለው አእምሮ የሚፈለገው እዚህ
ላይ ነው ፤ ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባ
ቸው ሰባት ተራራዎች ናቸው ፤ እንዲሁም
ሰባት ነገሥታት ናቸው ፤ 10አምስቱም ወድቀ
ዋል ፤ አንዱ አሁን አለ ፤ ሌላው ገና አልመ
ጣም ፤ እርሱ ሲመጣ ለጥቂት ጊዜ ብቻ መቆ
የት አለበት ። 11ስምንተኛው ንጉሥ ቀድሞ የነ
በረውና አሁን የሌለው አውሬ ነው ፤ እርሱ ከሰ
ባቱ አንዱ ነው ፤ ወደ ጥፋቱም ይሄዳል ።

12“ያየሃቸው ዐሥሩ ቀንዶች ገና ያልነገሡ
ዐሥር ነገሥታት ናቸው ፤ ነገር ግን ለአንዲት
ሰዓት ከአውሬው ጋር እንዲነግሡ የመንገሥ
ሥልጣን ያገኛሉ ። 13እነዚህ ዐሥር ነገሥታት
ተመሳሳይ አሳብ አላቸው ፤ እነርሱ ኀይላቸውንና
ሥልጣናቸውን ለአውሬው ያስረክባሉ ፤ 14እነ
ርሱ ከበጉ ጋር ጦርነት ያደርጋሉ ፤ ነገር ግን
በጉ የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ስለሆነ
ድል ይነሣቸዋል ፤ ከእርሱ ጋር ያሉት የተጠሩና
የተመረጡ የታመኑም አብረው ድል ይነሣሉ ።”

15መልአኩም እንዲህ አለኝ ፥ “አመንዝራ
ይቱ ተቀምጣባቸው ያየሃቸው ውሃዎች ሕዝቦ
ችና ፥ ሰዎች ፥ ወገኖችና ቋንቋዎች ናቸው ፤
16አውሬውና ያየሃቸው ዐሥር ቀንዶች አመንዝ
ራይቱን ይጠላሉ ፤ ወደ ጥፋት ያደርሱአታል ፤
ራቁትዋን ያስቀሩአታል ፤ ሥጋዋን ይበላሉ ፥
በእሳትም ያቃጥሏታል ፤ 17ዕቅዱን እንዲፈ
ጽሙ ይህን አሳብ በልባቸው ያኖረ እግዚአብ
ሔር ነው ፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል እስኪ
ፈጸም እነርሱ በአንድ አሳብ ይስማማሉ ፤ የመን
ገሥ ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ያስረክባሉ ።
18“ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ
የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት ።”

ምዕራፍ 18

የባቢሎን መውደቅ

1ከዚህ በኋላ ታላቅ ሥልጣን ያለው ሌላ
መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ ፤ ከክብሩ ነጸብ
ራቅ የተነሣ ምድር በራች ፤ 2በብርቱ ድምፅም
እንዲህ ሲል ጮኸ ፥ “ታላቂቱ ባቢሎን ወደ
ቀች! ወደቀች! የአጋንንት መኖሪያ ሆነች!
የርኵሳን መናፍስት ማደሪያ ሆነች! የሚያስጸይ
ፋና የሚያስጠሉ ወፎች መጠለያ ሆነች! 3ምክ
ንያቱም የሚያስከረውን የዝሙትዋን ወይን
ጠጅ ሕዝቦችን ሁሉ አጠጥታለች ፤ የምድር ነገ
ሥታት ከእርስዋ ጋር አመንዝረዋል ፥ የምድር
ነጋዴዎችም ከብዙ ምቾትዋ የተነሣ ሀብታ
ሞች ሆነዋል ።”

4ሌላ ድምፅም ከሰማይ እንዲህ ሲል ሰማሁ ፥
“ሕዝቤ ሆይ!
በኃጢአትዋ እንዳትተባበሩ ፤
የመቅሠፍትዋም ተካፋዮች
እንዳትሆኑ ፤
ከእርስዋ ውጡ ፤
5 ምክንያቱም የኃጢአትዋ ክምር
እስከ ሰማይ ደርሶአል ፤
እግዚአብሔር ዐመፃዋን
አስታውሶአል ፤
6 በሰጠችው መጠን ስጥዋት ፤
ባደረገችውም ሥራ እጥፍ ክፈልዋት ፤
እርስዋ በቀላቀለችበት ጽዋ ውስጥ
እጥፍ ኀይለኛ አድርጋችሁ
ቀላቅሉባት ፤
7 ለራስዋ ክብርና ምቾት የሰጠችውን
ያህል ፥
ሥቃይና ሐዘን ስጡአት ፤
እርስዋ በልብዋ
‘እንደ ንግሥት ተቀምጫለሁ ፤
መበለትም አይደለሁም ፤
ሐዘንም ከቶ አይደርስብኝም’ በማለት
ትመካለች ።
8 ስለዚህ መቅሠፍቶችዋ ሁሉ
በአንድ ቀን ይደርሱባታል ፤
ሞትና ሐዘን ረሀብም ይመጡባታል ፤
በእሳትም ትቃጠላለች ፤
ምክንያቱም በእርስዋ ላይ
የሚፈርድባት
ጌታ አምላክ ብርቱ ነው ።”

17፥4 ፡- ኤር. 51፥7 ። 17፥8 ፡- ዘፍ. 7፥7 ፡ ራእ. 11፥7 ፡ መዝ. 69፥28 ። 17፥12 ፡- ዘፍ. 7፥24 ።
18፥2 ፡- ኢሳ. 13፥21 ፡ 21፥9 ፡ ኤር. 50፥39 ፡ 51፥8 ፡ ራእ. 14፥8 ። 18፥3 ፡- ኢሳ. 23፥17 ፡ ኤር. 51፥7 ። 18፥4 ፡- ኢሳ. 48፥20 ፡
ኤር. 50፥8 ፡ 51፥6 ፡ 45 ። 18፥5 ፡- ዘፍ. 18፥20-21 ፡ ኤር. 51፥9 ። 18፥6 ፡- መዝ. 137፥8 ፡ ኤር. 50፥29 ።

9ከእርስዋ ጋር ያመነዘሩና በምቾት የኖሩ
የምድር ነገሥታት ፥ እርስዋ ስትቃጠል የሚወ
ጣውን ጢስ ሲያዩ ስለ እርስዋ እየጮኹ ያለት
ሳሉ ፤ 10ሥቃይዋንም በመፍራት በሩቅ ቆመው
“አንቺ ታላቂቱ ከተማ ፥ አንቺ ብርቱይቱ ከተማ
ባቢሎን ሆይ! ፍርድሽ በአንድ ሰዓት ውስጥ ስለ
መጣ ፥ ወዮልሽ! ወዮልሽ!” ይላሉ ።

11የመርከባቸውን ሞኒት ከእንግዲህ የሚገዛ
ስለሌለ የምድር ነጋዴዎችም ያለቅሱላታል ፤
ያዝኑላታልም ፤ 12በመርከባቸው የተጫነውም
“ወርቅ ፥ ብር ፥ የከበረ ድንጋይ ፥ ዕንቊ ፥
ቀጭን ልብስ ፥ ሐምራዊ ልብስ ፥ ሐር ልብስ ፥
ቀይ ልብስ ፥ መልካም መዓዛ ያለው እንጨት
ሁሉ ፥ ከዝሆን ጥርስ ፥ ውድ ከሆነ እንጨት ፥
ከነሐስ ፥ ከብረት ፥ ከእብነ በረድ የተሠራ ዕቃ
ሁሉ ፤ 13ቀረፋ ፥ ቅመም ፥ የሚሸት እንጨት ፥
ከርቤ ፥ ዕጣን ፥ ወይን ጠጅ ፥ የወይራ ዘይት ፥
ዱቄት ፥ ስንዴ ፥ ከብቶች ፥ በጎች ፥ ፈረሶች ፥
ሠረገላዎች ፥ ባሪያዎች ፥ ምርኮኞች” ነው ።
14ነጋዴዎቹም “ነፍስሽ የተመኘቻቸው መል
ካም ነገሮች ሁሉ ከእንቺ ርቀው ሄደዋል ፤ ሀብ
ትሽም ጌጣ ጌጥሽም ሁሉ ጠፍቶአል ፤ ከእንግ
ዲህ ወዲህ እነዚህን ሁሉ ከቶ አታገኛቸውም”
ይሉአታል ። 15እነዚህን ነገሮች ሁሉ እየገዙ
ሀብታሞች የሆኑ ነጋዴዎች ሥቃይዋን በመፍ
ራት በሩቅ ይቆማሉ ፤ እያለቀሱና እያዘኑም ፥
16“ቀጭን ልብስና ሐምራዊ ልብስ ቀይ ልብ
ስም ትለብስ የነበረች ፥ በወርቅና በከበረ ድን
ጋይ በዕንቊም ታሸበርቅ የነበረች ፤ ታላቂቱ
ከተማ ወዮላት! ወዮላት! 17ያን ያህል ሀብት
በአንድ ሰዓት ጠፋ” ይላሉ ።

የመርከብ አዛዦች ሁሉ ፥ በመርከብ
የሚጓዙ ሰዎች ሁሉ ፥ በመርከብ ላይ የሚሠሩ
ሁሉ ፤ በባሕር ላይ የሚነግዱ ሁሉ በሩቅ ይቆ
ማሉ ፤ 18እርስዋ ስትቃጠል የሚወጣውን ጢስ
ባዩ ጊዜ “ይህችን ታላቅ ከተማ የሚመስል ከቶ
ሌላ ከተማ ነበረን?” እያሉ ጮኹ ። 19በራሳ
ቸው ላይ አፈራ ነሰነሱ ፤ እያለቀሱና እያዘኑም
እንዲህ እያሉ ይጮኻሉ ፥ “በባሕር ላይ መርከ
ቦች ያላቸው ሁሉ በእርስዋ ሀብት ሀብታሞች
የሆኑ ፥ ያቺ ታላቅ ከተማ በአንድ ሰዓት ውስጥ
ስለወደመች ወዮላት! ወዮላት!”

20ሰማይ ሆይ! በእርስዋ ደስ ይበልህ! እና
ንተ ቅዱሳንና ሐዋርያት ነቢያትም ደስ ይበላ
ችሁ! ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለናንተ በእ
ርስዋ ላይ ፈርዶባታል ።

21ከዚህ በኋላ አንድ ብርቱ መልአክ ትልቅ
የወፍጮ ድንጋይ የሚያህል አንድ ድንጋይ አን
ሥቶ እንዲህ ሲል ወደ ባሕር ወረወረው ፥
“ታላቂቱ ከተማ ባቢሎን እንዲህ በኀይል ተገ
ፍታ ትወድቃለች ፤ ከእንግዲህ ወዲህም ከቶ
አትገኝም ፤ 22የበገና ደርዳሪዎችና የሙዚቀ
ኞች ድምፅ ፥ የዋሽንት ነፊዎችና የመለከት ነፊ
ዎች ድምፅ ፥ ዳግመኛ በአንቺ አይሰማም ፤ ማን
ኛውንም ዐይነት የእጅ ጥበብ የሚሠራ ብልኅ
ተኛ ሰው ከእንግዲህ ወዲህ በእንቺ አይገኝም ፤
የወፍጮም ድምፅ ከእንግዲህ በእንቺ አይሰ
ማም ። 23የመብራት ብርሃን ከእንግዲህ ወዲህ
በእንቺ አያበራም ፤ የሙሽራውና የሙሽራይቱ
ድምፅ ከእንግዲህ ወዲህ በእንቺ አይሰማም ፤
ነጋዴዎችሽ የዓለም ታላላቅ ሰዎች ነበሩ ፤ በአ
ስማትሽ ሕዝቦችን ሁሉ አሳስተሻል ።
24“በእርስዋ ውስጥ የነቢያትና የቅዱሳን ፥
በምድር ላይ የተገደሉ ሰዎች ሁሉ ደም ተገኝ
ቶአል ።”

ምዕራፍ 19

1ከዚህ በኋላ እንዲህ የሚል የብዙ ሰዎችን
ድምፅ የሚመስል ታላቅ ድምፅ በሰማይ ሰማሁ
“ሃሌ ሉያ! ማዳንና ክብር ኀይልም የአምላካ
ችን ነው ፤ 2ምክንያቱም ፍርዱ እውነትና ትክ
ክል ነው ፤ ምድርን በዝሙትዋ ያረከሰችውን
ታላቂቱን አመንዝራ በፍርድ ቀጥቶአታል ፤ እር
ስዋን በመቅጣትም የአገልጋዮቹን ደም ተበቅሎ
አል ፤ 3እንደገናም ፥ ሃሌ ሉያ! ጢስዋ ለዘላለም
ወደ ላይ ይወጣል!” እያሉ ጮኹ ። 4ሃያ
አራቱ ሽማግሌዎችና አራቱ እንስሶች በዙፋኑ
ላይ ለተቀመጠው አምላክ በግምባራቸው ተደፍ
ተው “አሜን ፥ ሃሌ ሉያ!” እያሉ ሰገዱ ።

የበጉ ሠርግ ግብዣ

5ከዚህ በኋላ “እርሱን የምትፈሩ አገልጋዮቹ
ሁሉ ፥ ታናናሾችም ታላላቆችም ፤ አምላካችንን
አመስግኑ” የሚል ድምፅ ከዙፋኑ ወጣ ።
6የብዙ ሰዎችን ድምፅ ፥ የወራጅ ውሃን ድምፅ ፥
የብርቱ ነጐድጓድንም ድምፅ ፥ የሚመስል
ድምፅ እንዲህ ሲል ሰማሁ ፥ “ሁሉን የሚችል
ጌታ አምላካችን ስለ ነገሠ ሃሌ ሉያ! 7የበጉ
ሠርግ ስለደረሰና የእርሱም ሙሽራ ስለ ተዘጋ
ጀች ደስ ይበለን ፤ ደስታም እናድርግ

18፥9-10 ፡- ሕዝ. 26፥16-17 ። 18፥11 ፡- ሕዝ. 27፥31-36 ። 18፥12-13 ፡- ሕዝ. 27፥12 ፡ 13 ፡ 22 ።
18፥15 ፡- ሕዝ. 27፥31 ፡ 36 ። 18፥17 ፡- ኢሳ. 23፥14 ፡ ሕዝ. 27፥26-30 ። 18፥18 ፡- ሕዝ. 27፥32 ።
18፥19 ፡- ሕዝ. 27፥30-34 ። 18፥20 ፡- ዘፍ. 32፥43 ፡ ኤር. 51፥48 ። 18፥21 ፡- ኤር. 51፥63-64 ፡ ሕዝ. 26፥21 ።
18፥22 ፡- ሕዝ. 26፥13 ፡ ኢሳ. 24፥8 ። 18፥22-23 ፡- ኤር. 7፥34 ፡ 25፥10 ። 18፥24 ፡- ኤር. 51፥49 ።
19፥2 ፡- ዘፍ. 32፥43 ፡ 2ነገ. 9፥7 ። 19፥3 ፡- ኢሳ. 34፥10 ። 19፥5 ፡- መዝ. 115፥13 ። 19፥6 ፡- ሕዝ. 1፥24 ፡
መዝ. 93፥1 ፡ 97፥1 ፡ 99፥1 ።

እናክብረውም ፤ [8] የሚያንጸባርቅና ንጹሕ የሆነ
ቀጭን ልብስ እንድትለብስ ተሰጣት ፤ ቀጭኑ
ልብስ የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ ነው ።”
[9] ከዚህ በኋላ መልአኩ “ወደ በጉ ሠርግ
ግብዣ የተጠሩ ዕድለኞች ናቸው ብለህ ጻፍ”
አለኝ ፤ ቀጥሎም “ይህ የእግዚአብሔር እውነ
ተኛ ቃል ነው” አለ ።
[10] እኔም ለመልአኩ ልሰግድለት በእግሩ ሥር
በግምባሬ ተደፋሁ ፤ እርሱ ግን “ተው! ይህን
አታድርግ! እኔም እኮ ከአንተና የኢየሱስን ምስ
ክርነት ከያዙት ወንድሞችህ ጋር አገልጋይ ነኝ ፤
ለእግዚአብሔር ስገድ ፤ ምክንያቱም የኢየሱስ
ምስክርነት የትንቢት መንፈስ ነው” አለኝ ።

በነጩ ፈረስ ላይ የተቀመጠ ፈረሰኛ

[11] ከዚህ በኋላ ሰማይ ተከፍቶ አየሁ ፤ እነሆ
ነጭ ፈረስም አየሁ ፤ በፈረሱ ላይ የተቀመጠው
ታማኝና እውነተኛ የሚባል ነው ፤ እርሱ በትክ
ክል ይፈርዳል ይዋጋልም ፤ [12] ዐይኖቹ የእሳት ነበ
ልባል ይመስላሉ ፤ በራሱም ላይ ብዙ ዘውዶች
አሉ ፤ ከእርሱ በቀር ሌላ ማንም የማያውቀው በእ
ርሱ ላይ የተጻፈ ስም ነበረ ፤ [13] እርሱ በደም የተነ
ከረ ልብስ ለብሶ ነበር ፤ ስሙም “የእግዚአብሔር
ቃል” የሚባል ነው ። [14] በነጫጭ ፈረሶች ላይ
የተቀመጡ ፥ ነጭና ንጹሕ የሆነ ቀጭን ልብስ
የለበሱ የሰማይ ሠራዊት ተከትለውታል ፤ [15] ሕዝ
ቦችን የሚመታበት ስለታም ሰይፍ ከአፉ ወጣ ፤
በብረት በትርም ይገዛቸዋል ፤ እርሱ ሁሉን የሚ
ችለውን የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣ መግለጫ
የሆነውን የወይን ጠጅ መጭመቂያ ይረግጣል ፤
[16] በልብሱና በጭኑ ላይ “የነገሥታት ንጉሥ ፥
የጌቶች ጌታ” የሚል ስም ተጽፎአል ።
[17] ከዚህ በኋላ በፀሐይ ላይ የቆመ አንድ
መልአክ አየሁ ፤ እርሱ በሰማይ ለሚበርሩ
ወፎች እንዲህ ሲል በታላቅ ድምፅ ጮኸ ፥
“ወደ ታላቁ የእግዚአብሔር ግብዣ ኑ ተሰብ
ሰቡ ፤ [18] የነገሥታትን ሥጋ ፥ የጦር አዛዦችን
ሥጋ ፥ የብርቱ ጦረኞችን ሥጋ ፥ የፈረሶችንና
የፈረሰኞችን ሥጋ ፥ የጌቶችንና የአገልጋዮችን
ሥጋ ፥ የታናናሾችንና የታላላቆችን ሥጋ ፥ የማ
ንኛውንም ሰው ሁሉ ሥጋ ኑ ብሉ ።”
[19] እንዲሁም አውሬውና የምድር ነገሥታት
ወታደሮቻቸውም በነጩ ፈረስ ላይ ከተቀመጠ
ውና ከሠራዊቱ ጋር ለመዋጋት ተሰብስበው
አየሁ ፤ [20] ነገር ግን አውሬው ተያዘ ፤ ከእርሱም
ጋር በፊቱ ብዙ ተአምራት ያደርግ የነበረው
ሐሰተኛው ነቢይ ተያዘ ፤ እርሱ የአውሬው
ምልክት የነበረባቸውንና ለአውሬውም ምስል
ይሰግዱ የነበሩትን ተአምራት እያደረገ ያስታ
ቸው ነበር ፤ እነዚህ ሁለቱ በዲን ወደሚቃጠ
ለው የእሳት ባሕር ከነሕይወታቸው ተጣሉ ።
[21] የቀሩት ደግሞ በነጩ ፈረስ ላይ ከተቀመ
ጠው አፍ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ ፤ ወፎ
ችም ሁሉ ሥጋቸውን በመብላት ጠገቡ ።

ምዕራፍ 20

የሺ ዓመቱ መንግሥት

[1] ከዚህ በኋላ የጥልቁን ጉድጓድ መክፈቻና
ትልቅ ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ
ሲወርድ አየሁ ፤ [2] ዘንዶውንም ይዞ ሺ ዓመት
አሰረው ፤ ይህም ዘንዶ ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን
የሚባለው የቀድሞው እባብ ነው ፤ [3] ሺው ዓመት
እስኪፈጸም ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ ሕዝቦችን
እንዳያስት መልአኩ ዘንዶውን ወደ ጥልቁ
ጉድጓድ ጣለው ፤ ዘግቶም በማኅተም አሸገው ፤
ከዚያ በኋላ ለጥቂት ጊዜ መፈታት ይገባዋል ።
[4] ከዚህ በኋላ ዙፋኖችን አየሁ ፤ በዙፋኖቹም
ላይ የመፍረድ ሥልጣን የተሰጣቸው ተቀምጠው
አየሁ ፤ ስለ ኢየሱስ ምስክርነትና ስለ እግዚአብ
ሔር ቃል ራሶቻቸው የተቈረጡባቸውን ሰዎች
ነፍሶች አየሁ ፤ እነርሱ ለአውሬውና ለምስሉ ያል
ሰገዱ ፤ ምልክቱንም በግምባራቸውም ሆነ በእጃ
ቸው ላይ ያላደረጉ ናቸው ፤ እነርሱ ከሞት ተነሥ
ተው ከክርስቶስ ጋር ሺ ዓመት ነገሡ ። [5] የቀሩት
ሙታን ግን ሺው ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ከሞት
አልተነሡም ፤ ይህም የመጀመሪያው ትንሣኤ
ነው ፤ [6] የመጀመሪያው ትንሣኤ ተካፋይ የሆኑ
የተመሰገኑና ቅዱሳን ናቸው ፤ ሁለተኛው ሞት
በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም ፤ እነርሱ የእግዚ
አብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ፤ ከክርስቶ
ስም ጋር ሺ ዓመት ይነግሣሉ ።

የሰይጣን መሸነፍ

[7] ሺው ዓመት ከተፈጸመ በኋላ ሰይጣን ከእስ
ራቱ ይፈታል ፤ [8] በዓለም ሁሉ የሚገኙትን ፥
ጎግና ማጎግ የሆኑትን ሕዝቦች ሊያስትና ለጦርነ
ትም ሊያስከትት ይወጣል ፤ ቍጥራቸው በባሕር
ዳር እንዳለ አሸዋ ነው ፤ [9] እነርሱ ወደ ምድር
ሁሉ ተሠራጭተው የቅዱሳንን ሰፈርና የተወደደ
ችውን ከተማ ከበቡ ፤ ነገር ግን እሳት ከሰማይ
ወርዶ በማቃጠል ደመሰሳቸው ። [10] ያሳታቸው
ዲያብሎስ ፥ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉ
በት በዲን በሚቃጠል እሳት ባሕር ውስጥ
ተጣሉ ፤ ሌሊትና ቀን ለዘላለም ይሠቃያሉ ።

የመጨረሻ ፍርድ

[11] ከዚህ በኋላ ታላቅ ነጭ ዙፋንና በዙፋ
ኑም ላይ የተቀመጠውን አየሁ ፤ ምድርና ሰማይ
ከፊቱ ሸሹ ፤ ስፍራም አልተገኘላቸውም ፤
[12] ታናናሾችንና ታላላቆችን ሙታን በዙፋኑ
ፊት ቆመው አየሁ ፤ መጻሕፍትም ተከፈቱ ፤
የሕይወት መጽሐፍ የሆነ ሌላ መጽሐፍም ተከ
ፈተ ፤ ሙታንም በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው
ሥራቸው መሠረት ፍርድ ተቀበሉ ፤ [13] ባሕርም
በውስጡ ያሉትን ሙታን ሰጠ ፤ ሞትና ሲኦ
ልም በእነርሱ ውስጥ የነበሩትን ሙታን ሰጡ ፤
እያንዳንዱም ሰው በሥራው መሠረት ፍርድ
ተቀበለ ። [14] ሞትና ሲኦልም ወደ እሳት ባሕር
ተጣሉ ፤ ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት
ነው ፤ [15] ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያል
ተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ተጣለ ።

ምዕራፍ 21

አዲሱ ሰማይና አዲሲቱ ምድር

[1] ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር
አየሁ ፤ ምክንያቱም የመጀመሪያው ሰማይና
የመጀመሪያይቱ ምድር አልፈው ነበር ፤ ባሕ
ርም ከእንግዲህ ወዲህ አልነበረም ፤ [2] ቅድስቲቱ
ከተማ ፥ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ፥ ለባልዋ እንዳጌ
ጠች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር
ዘንድ ስትወርድ አየሁ ፤ [3] እንዲህም የሚል
ታላቅ ድምፅ ከዙፋኑ ሲወጣ ሰማሁ ፥ “እነሆ
የእግዚአብሔር ማደሪያ ከሰዎች ጋር ነው ፤ ከእ
ነርሱም ጋር ይኖራል ፤ እነርሱም የእርሱ
ሕዝብ ይሆናሉ ። እግዚአብሔር ራሱ ከእነርሱ
ጋር ይሆናል ፤ አምላካቸውም ይሆናል ፤ [4] እን
ባን ሁሉ ከዐይናቸው ላይ ይጠርጋል ፤ ሞት
ወይም ሐዘን ወይም ለቅሶ ወይም ሥቃይ ከእን
ግዲህ ወዲህ አይኖርም ፤ ምክንያቱም የቀድሞ
ዎቹ ነገሮች ሥርዓት አልፎአል ።”
[5] በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውም “እነሆ እኔ
ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ” አለ ፤ ቀጥ
ሎም “ይህ ቃል የታመነና እውነት ስለሆነ
ጻፍ” አለኝ ። [6] ከዚህም በኋላ እንዲህ አለኝ ፥
“ተፈጸመ! አልፋና ዖሜጋ ፥ የመጀመሪያውና
የመጨረሻው እኔ ነኝ ፤ ለተጠማ ከሕይወት
ውሃ ምንጭ ያለ ምንም ዋጋ በነፃ እሰጠዋ
ለሁ ፤ [7] ድል የነሣ ይህን ይወርሳል ፤ እኔ አም
ላክ እሆነዋለሁ ፤ እርሱም ልጄ ይሆናል ፤
[8] ነገር ግን ፈሪዎች ፥ እምነተ ቢሶች ፤ ርኵ
ሶች ፥ ነፍሰ ገዳዮች ፥ አመንዝሮች ፥ አስማተ
ኞች ፥ ጣዖት አምላኪዎች ፥ ውሸታሞች ሁሉ
ዕጣ ክፍላቸው በዲን በሚቃጠለው በእሳት
ባሕር ውስጥ ይሆናል ፤ ይህም ሁለተኛው
ሞት ነው ።”

አዲሲቱ ኢየሩሳሌም

[9] የመጨረሻዎቹ ሰባት መቅሠፍቶች የሞሉባ
ቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእ
ክት አንዱ መጥቶ “ና የበጉ ሚስት የሆነችውን
ሙሽራይቱን አሳይሃለሁ” አለኝ ። [10] በመንፈ
ስም ወደ አንድ ትልቅ ረዥም ተራራ ወሰደኝና
ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ፥ ከእግዚአብሔር
ዘንድ ከሰማይ ስትወርድ አሳየኝ ፤ [11] በእግዚአብ
ሔር ክብር ታበራ ነበር ፤ የብርሃንዋም ድም
ቀት እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ ፥ እንደ እያሰ
ጲድ ዕንቊና እንደ ብሩህ መስተዋት የጠራ
ነበረ ፤ [12] ዐሥራ ሁለት ደጃፎች ያሉት ታላቅና
ረዥም የግንብ አጥር ነበራት ፤ በዐሥራ ሁለ
ቱም ደጃፎች ዐሥራ ሁለት መላእክት ቆመው
ነበር ፤ በደጃፎቹም ላይ የዐሥራ ሁለቱ የእስራ
ኤል ነገዶች ስሞች ተጽፈውባቸው ነበር ።
[13] በምሥራቅ ሦስት ደጃፎች በሰሜን ሦስት
ደጃፎች ፥ በደቡብ ሦስት ደጃፎች ፥ በምዕራብ
ሦስት ደጃፎች ነበሩ ። [14] የከተማይቱ የግንብ
አጥር ዐሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩት ፤ በመሠ
ረቶቹም ላይ የዐሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት
ስሞች ተጽፈው ነበር ፤ [15] የተናገረኝም መል
አክ ከተማይቱንና ደጃፎችዋን ፥ የግንቡንም
አጥር የሚለካበት የወርቅ ዘንግ ነበረው ፤ [16] ከተ
ማይቱም ርዝመትዋና ስፋትዋ እኩል የሆነ የአ
ራት ማእዘን ቅርጽ ነበራት ፤ መልአኩ ከተማይ
ቱን በመለኪያው ዘንግ ለካትና ርዝመትዋ
ሁለት ሺ አራት መቶ ኪሎ ሜትር ያህል ሆነ ፤
ስፋትዋና ከፍታዋም ያንኑ ያህል ሆነ ፤ [17] መል
አኩ የግንቡን አጥር ለካ ፤ መልአኩ በሚለካበት
በታወቀው መለኪያ ልክ ሰባ ሁለት ሜትር
ያህል ሆነ ፤ [18] ግንቡም የተሠራው ከኢያሰጲድ
ነበረ ፤ ከተማይቱም እንደ መስተዋት በጠራ በን
ጹሕ ወርቅ የተሠራች ነበረች ፤ [19] የከተማይቱ
ግንብ መሠረቶች በልዩ ልዩ የከበረ ድንጋይ
ያጌጡ ነበሩ ፤ የመጀመሪያው መሠረት ኢያሰ
ጲድ ነበረ ፤ ሁለተኛው ሰንፔር ፥ ሦስተኛው
ኬልቄዶን ፥ አራተኛው መረግድ ፥ [20] አምስተ
ኛው ሰርዶንክስ ፥ ስድስተኛው ሰርድዮን ፤ ሰባ
ተኛው ክርስቲሎቤ ፥ ስምንተኛው ቢረሌ ፥ ዘጠ
ኛው ወራውሬ ፥ ዐሥረኛው ክርስጵራስስ ፥
ዐሥራ አንደኛው ያክንት ፥ ዐሥራ ሁለተኛው
አሜቴስጢኖስ ነበረ ። [21] ዐሥራ ሁለቱም ደጃ
ፎች ፤ ዐሥራ ሁለት ዕንቊዎች ነበሩ ፤ እያንዳ
ንዱ ደጃፍ ከአንድ ዕንቊ የተሠራ ነበረ ፤ የከተ
ማይቱም መንገድ እንደ መስተዋት ብርሃን የሚ
ያስተላልፍ ንጹሕ ወርቅ ነበረ ።

19:9 ፡- ማቴ. 22:2-3 ። 19:11 ፡- ሕዝ. 1:1 ፡ መዝ. 96:13 ፡ ኢሳ. 11:4 ። 19:12 ፡- ዳን. 10:6 ። 19:15 ፡- መዝ. 2:9 ፡ ኢሳ. 63:3 ፡ ኤፌሳ 3:13 ፡ ራእ. 14:20 ። 19:17-18 ፡- ሕዝ. 39:17-20 ። 19:20 ፡- ራእ. 13:1-18 ። 20:2 ፡- ዘፍ. 3:1 ። 20:4 ፡- ዳን. 7:9 ፡22 ። 20:8 ፡- ሕዝ. 7:2 ፡ 38:2 ፡9 ፡15 ። 20:11-12 ፡- ዳን. 7:9-10 ።

21:1 ፡- ኢሳ. 65:17 ፡ 66:22 ፡ 2ጴጥ. 3:13 ። 21:2 ፡- ኢሳ. 52:1 ፡ 61:10 ፡ ራእ. 3:12 ። 21:3 ፡- ሕዝ. 37:27 ፡ ዘሌ. 26:11-12 ። 21:4 ፡- ኢሳ. 25:8 ፡ 35:10 ፡ 65:19 ። 21:6 ፡- ኢሳ. 55:1 ። 21:7 ፡- 2ሳሙ. 7:14 ፡ መዝ. 89:26-27 ። 21:10 ፡- ሕዝ. 40:2 ። 21:12-13 ፡- ሕዝ. 48:30-35 ። 21:15 ፡- ሕዝ. 40:3 ። 21:18-21 ፡- ኢሳ. 54:11-12 ።

22 ሁሉን የሚችል ጌታ አምላክና በጉ የእር
ስዋ መቅደስ ስለሆኑ በከተማይቱ ውስጥ መቅ
ደስ አላየሁም ፤ 23 የእግዚአብሔር ክብር ስለሚ
ያበራላትና በጉ መብራትዋ ስለሆነ ከተማይቱ
ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጋ
ትም ። 24 ሕዝቦች በብርሃንዋ ይመላለሳሉ ፤ የም
ድር ነገሥታትም ክብራቸውን ወደ እርስዋ
ያመጣሉ ፤ 25 በዚያ ሌሊት ስለሌለ ደጆቹዋ
በማንኛውም ቀን አይዘጉም ። 26 የመንግሥታት
ግርማና ክብር ወደ እርስዋ ይገባሉ ፤ 27 ጸያፍ
የሆነ ነገር ከቶ ወደ እርስዋ አይገባም ፤ ርኵሰ
ትን የሚያደርግና ውሸት የሚናገር ከቶ ወደ
እርስዋ አይገባም ፤ ወደ እርስዋ የሚገቡ ፥ ስሞ
ቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ የተጻፉ ብቻ
ናቸው ።

ምዕራፍ 22

1 ከዚህ በኋላ መልአኩ ከእግዚአብሔርና
ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብሩህ መስተ
ዋት የጠራውን የሕይወት ውሃ ወንዝ አሳየኝ ፤
2 ይህ ወንዝ በከተማይቱ ዋና መንገድ መካከል
ሰንጥቆ ያልፋል ፤ በወንዙ ግራና ቀኝ በየወሩ
እያፈራ ፥ በዓመት ዐሥራ ሁለት ጊዜ ፍሬ የሚ
ሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ ፤ የዛፉም ቅጠሎች
ሕዝቦችን ይፈውሱ ነበር ፤ 3 ከእንግዲህም ወዲህ
ምንም ዐይነት እርግማን አይኖርም ፤ የእግዚአ
ብሔርና የበጉ ዙፋን በከተማይቱ ውስጥ ይሆ
ናል ፤ አገልጋዮቹም ያመልኩታል ፤ 4 ፊቱን
ያያሉ ፤ ስሙም በየግምባራቸው ላይ ይሆናል ፤
5 ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይኖርም ፤ ጌታ
አምላክ ስለሚያበራላቸው የመብራት ወይም
የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም ፥ ለዘላለምም
ይነግሣሉ ።

የኢየሱስ መምጣት

6 ከዚህ በኋላ መልአኩ እንዲህ አለኝ ፥ “እነ
ዚህ ቃላት የታመኑና እውነተኞች ናቸው ፤
መንፈሱን ለነቢያት የሚሰጥ ጌታ አምላክ ከጥ
ቂት ጊዜ በኋላ የሚሆኑትን ነገሮች ለአገልጋ
ዮቹ ለመግለጥ መልአኩን ላከ ።”
7 ኢየሱስም “እነሆ ፥ እኔ በቶሎ እመጣ
ለሁ ፤ የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል የሚፈ
ጽም የተመሰገነ ነው” አለ ።
8 እነዚህን ነገሮች የሰማሁና ያየሁ እኔ ዮሐ
ንስ ነኝ ፤ እነዚህን ነገሮች በሰማሁና ባየሁ
ጊዜ ፥ እነዚህን ነገሮች ላሳየኝ መልአክ ልሰግድ
ለት በእግሩ ሥር ወደቅሁ ። 9 መልአኩ ግን
“ተው ይህን አታድርግ! እኔ ከአንተና ከወንድ
ሞችህ ከነቢያት ጋር ፥ የዚህን መጽሐፍ ቃል
ከሚፈጽሙ ሰዎች ጋር አገልጋይ ነኝ ፤ ለእግዚ
አብሔር ስገድ!” አለኝ ። 10 ቀጥሎም እንዲህ
አለኝ ፥ “ጊዜው አጭር ስለሆነ የዚህን መጽ
ሐፍ የትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው ፥
11 ከእንግዲህ ወዲህ ዐመፀኛው ማመፁን ይቀ
ጥል ፤ ርኵሱም ይርከስ ፤ ጻድቁም ይጽደቅ ፥
ቅዱሱም ይቀደስ ።”
12 “እነሆ እኔ በቶሎ እመጣለሁ ፤ ለእያንዳ
ንዱ እንደ ሥራው የምሰጠውን ዋጋ ይዣለሁ ፤
13 አልፋና ያሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው ፥ መጀ
መሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ ።”
14 ከሕይወት ዛፍ ፍሬ ለመብላትና በደጆ
ቹዋም ወደ ከተማይቱ ለመግባት መብት እንዲ
ኖራቸው ልብሳቸውን ያጠቡ ዕድለኞች
ናቸው ። 15 ነውረኞች ፥ አስማተኞች ፥ አመንዝ
ራዎች ፥ ነፍሰ ገዳዮች ፥ ጣዖት አምላኪዎች ፥
ውሸትን የሚወድዱና የሚናገሩ ሁሉ ከከተማ
ይቱ ውጭ ይሆናሉ ።
16 “እኔ ኢየሱስ ይህን ምስክርነት እንዲሰጣ
ችሁ መልአኬን ለአብያተ ክርስቲያናት ልኬአ
ለሁ ፥ እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ ፤ የሚያበራ
የንጋት ኮከብ ነኝ ።”
17 መንፈስ ቅዱስና ሙሽራይቱ “ና”
ይላሉ ፤ የሚሰማም “ና” ይበል ፥ የተጠማም
ይምጣ ፥ የፈለገም የሕይወትን ውሃ ያለ ምንም
ዋጋ በነፃ ይውሰድ ።
18 እነሆ በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትን
ቢት ቃል የሚሰማውን ሁሉ አስጠነቅቃለሁ ፥
ማንም በዚህ ቃል ላይ አንዳች ነገር ቢጨ
ምር ፥ በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍ
ቶች እግዚአብሔር ይጨምርበታል ። 19 ማንም
በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች
አንዳች ነገር ቢያጐድል ፥ በዚህ መጽሐፍ
ከተነገሩት ከሕይወት ዛፍ ፍሬና ከቅድስቲቱ
ከተማ እግዚአብሔር ድርሻውን ያጐድልበ
ታል ።
20 የእነዚህ ነገሮች ምስክር የሆነው “አዎ!
በቶሎ እመጣለሁ” ይላል ።
አሜን ፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና!
21 የጌታ የኢየሱስ ጸጋ ከሁላችሁ* ጋር
ይሁን ፤ አሜን ።

1* 22:21 ከሁላችሁ ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “ከሁሉ” ሲሉ ፥ ሌሎች “ከእግዚአብሔር ሕዝብ” ይላሉ ፥ “ከእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ” የሚሉም አሉ ።

21:23 ፦ ኢሳ. 60:19-20 ። 21:24 ፦ ኢሳ. 60:3 ። 21:25-26 ፦ ኢሳ. 60:11 ። 21:27 ፦ ኢሳ. 52:1 ፥ ሕዝ. 44:9 ።
22:1 ፦ ሕዝ. 47:1 ፥ ዘካ. 14:8 ። 22:2 ፦ ዘፍ. 2:9 ፥ ሕዝ. 47:12 ። 22:3 ፦ ዘካ. 14:11 ። 22:5 ፦ ኢሳ. 60:19 ፥ ዳን. 7:18 ። 22:11 ፦ ዳን. 12:10 ። 22:12 ፦ ኢሳ. 40:10 ፥ 62:11 ፥ መዝ. 28:4 ፥ ኤር. 17:10 ።
22:13 ፦ ራእ. 1:8,17 ፥ 2:8 ፥ ኢሳ. 44:6 ፥ 48:12 ። 22:14 ፦ ዘፍ. 2:9 ፥ 3:22 ። 22:16 ፦ ኢሳ. 11:1,10 ።
22:17 ፦ ኢሳ. 55:1 ። 22:18-19 ፦ ዘዳ. 4:2 ፥ 12:32 ።

ካርታዎች
የቃላት መፍቻ
የቃላት ንጽጽር



አብርሃም
የተዘዋወረባቸው አገሮች


1. ሮቤል
2. ስምዖን
3. ይሁዳ
4. ዛብሎን
5. ይሳኮር
6. ዳን
7. ጋድ
8. አሴር
9. ንፍታሌም
10. ኤፍሬም
11. ምናሴ
12. ብንያም
ሜዲትራኒያን
ገሊላ
ጎላን
ባሳን
ገለዓድ
ሞአብ
ዕሞን
ዕረብ
ከነዓናውያን
ፍልስጥኤም
ሊቃውያን
ኤዶም
ሰሜን
ከሎሜትር
5 10 20 40 60 80
የእስራኤል ነገዶች
የሰፈሩባቸውን ቦታዎች የሚያሳይ
የእስራኤል አገር ካርታ


ሜዲትራኒያን
ገሊላ
ጎላን
ዕሥር ከተማ
ሰማርያ
ይሁዳ
ኤዶምያስ
ሰሜን
ከሎሜትር
5 10 20 40 60 80
የእስራኤል አገር
በዐዲስ ኪዳን ዘመን

ሐዋርያው ጳውሎስ
የተዘዋወረባቸው አገሮች
ጣሊያ
ደልማጥያ
መቄዶንያ
ቢታንያ
ጳንጦስ
ሮም
ምስት ማደሪያዎች
አፍዮስ ገበያ
ፎቲዮሉ
ሲራኩስ
ሬጊዮም
ኔፕልስ
ፖሪዎስ
ቆሮንቶስ
ኤቶልያ
ኤጌዎስ
ተሰሎንቄ
ቤርያ
ፊልጵስዩስ
ጢሮአስ
ኦሊ
ኤርጋሞ
ትያጥሮስ
ሰርዴስ
ፊላደልፍያ
ሰምርኔስ
ላኦዲቅያ
ሎዶትያ
ፍላስደስ
ኤፌሶን
ሚሌጦ
ኮስ
ሮዶስ
ፋጥራ
ፓጥራ
ቀጵሮስ
ሳላሚስ
ፍኖ
ሳልሞን
ቀርጤስ
ቀጵሮስ
ሳላሚስ
ፓፎስ
ሊዶ
ጢሮስ
ፕጦሌማይስ
ቂሣሪያ
ኢየሩሳሌም
ደማስቆ
ሊስጥራ
ደርቤ
ጠርሴስ
ሊኩቃስ
ኢኮንዮ
ፒሲዲያ
ፍርጊያ
ገላትያ
ቀጳዶቅያ
ሶርያ
ኤፍራጥስ
ጢግሮስ
ሜሶጶጣሚያ
ሜድትራኒያን
ከሬና
ግብጽ
ዐረብ
ኢስከንድርያ
ሰሜን
ኪሎሜትር
50 100 200 300 400

የቃላት መፍቻ

ሄሶጵ ፦ በአይሁድ ሥርዓት ደም የሚረጭበት ብዙ ቅርንጫፍ ያለው አነስተኛ ተክል (ዘጸ. 12 ፡22) ።

ሊቀካህናት ፦ የአይሁድ ካህናትን የሚቈጣጠር የካህናት አለቃ ፤ የዋናው ሸንጎ ሊቀ መንበር በመሆንም ያገለግል ነበር ፤ በዓመት አንድ ጊዜ በኃጢአት ማስተስረያ ቀን ልዩ መሥዋዕት ያቀርባል ፤ በዚህም ቀን ብቻ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ ስለራሱና ስለሕዝቡ ኃጢአት ስርየት በታቦቱ ላይ ደም ይረጫል ።

ሌዋታን ፦ በአፈ ታሪክ የሚነገርለት በጥንት ዘመን በባሕር ውስጥ ይኖር የነበረ አዞ የሚመስል በጣም ትልቅ ዘንዶ ነው ፤ እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት የነበረው ቅጥየለሽ ሁኔታ በሌዋታን ይመሰላል (ኢሳ. 27 ፡1 ፤ መዝ. 74 ፡14) ።

ሌዋዊ ፦ 1. ከሌዊ ነገድ የሆነ ሰው ። 2. በመንፈሳዊ አገልግሎት ካህንን የሚረዳ ሰው ።

ሐዋርያ ፦ በተለይ ኢየሱስ ፡ እርሱን እንዲከተሉና እንዲረዱት ለመረጣቸው ፡ሥራ ሁለት ሰዎች ለእያንዳንዱ የተሰጠ ስም ነው ፤ ይሁን እንጂ ይህ ስም ለጳውሎስና ለእንዳንድ የክርስቶስ አገልጋዮችም ተሰጥቶአል ፤ የቃሉም ፍች "ለመንጌል ሥራ የተላከ" ማለት ነው ።

ሔርሜን ፦ በግሪክ ሃይማኖት የዋናው አምላክ ጓደኛና መልእክተኛ ተብሎ ይታመንበት የነበረ ሐሰተኛ አምላክ ነው (ሐ.ሥ. 14 ፡12-13) ።

መሥዋዕት ፦ ሰው ለአምላኩ አንዳች ነገር ሲያቀርብ ወይም ሲያቅዋል ፡ ያ ነገር መሥዋዕት ወይም ቍርባን ይባላል ። አስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ከሚያቀርቡአቸው ዋናዎቹ መሥዋዕቶች መካከል የሚቃጠል መሥዋዕትና ለደኅንነት የሚሆን የኅብረት መሥዋዕት የተባሉት ናቸው ። 1. የሚቃጠል መሥዋዕት ፦ ለዚህ ዐይነቱ መሥዋዕት የሚታረደው እንስሳ ሙሉ በሙሉ በመሠዊያው ላይ ይቃጠላል ። 2. ለደኅንነት የሚሆን የኅብረት መሥዋዕት ፦ ለዚህ ዐይነቱ መሥዋዕት የሚቀርበው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ለመጠበቅ ወይም ለማደስ ነው ፤ ከታረደው እንስሳ ክፊሉ ተወስዶ በመሠዊያው ላይ ይቃጠላል ፤ ቀሪውን ክፍል ግን ካህናቱ ወይም ምእመናኑ ይበሉታል ።

ሞሌክ ፦ ጥንታውያን የሆኑ የከነዓን ሕዝቦች ያመልኩአቸው ከነበሩ ጣዖቶች አንዱ ነው ።

ሰርዲኖን ፦ ቀለሙ ቀይ የሆነ የከበረ ድንጋይ ነው ።

ሰርዶንክስ ፦ የተለያየ ቀለም ያለው የከበረ ድንጋይ ።

ሰንበት ፦ በዕብራይስጥ የቃሉ ትርጉም "ማቆም ፡ መተው" ማለት ነው ፤ የሳምንቱ ሰባተኛ ቀን ሲሆን ፡ በአይሁድ እምነት በዚህ ቀን ሥራ አይሠራም ።

ሰንፔር ፦ ቀለሙ ሰማያዊ ፡ እጅግ ውድ የሆነ የከበረ ድንጋይ ።

ሰዱቃውያን ፦ ከአይሁድ ሃይማኖት ወገኖች አንዱ ክፍል ናቸው ፤ አብዛኛዎቹ ካህናት ነበሩ ፤ የእምነታቸው መሠረት የሚያደርጉት በብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎችን አምስት መጻሕፍት ብቻ ነበር ፤ በትንሣኤ ሙታን አያምኑም ነበር ፤ እንዲሁም ከፈሪሳውያን የተለየ ብዙ እምነት ነበራቸው ፤ ብዙ ጊዜ ሊቀ ካህናት ከእነርሱ ይመረጥ ነበር ፤ ከአይሁድ ሸንጎም የሚበዙት ሰዱቃውያን ነበሩ ።

ሲዋን ፦ በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር ሦስተኛው ወር ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር የግንቦት ወር መሆኑ ነው ።

ሳምራውያን ፦ በይሁዳና በገሊላ መካከል ትገኝ የነበረች የሰማርያ ግዛት ተወላጆች ናቸው ፤ በሥለቲካ ፡ በዘር ፡ በባሕልና በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት በአይሁዳውያንና በሳምራውያን መካከል ብዙ ቅራኔ ነበር ፤ ሳምራውያን አሪትን እንጂ ነቢያትን አይቀበሉም ነበር ፤ የአምልኮ ቦታቸውም በኢየሩሳሌም ሳይሆን በገሪዛን ነበር ።

ሸባጥ ፦ በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር ዐሥራ አንደኛው ወር ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር የየካቲት ወር መሆኑ ነው ።

ሸንጎ ፡- በጥንታዊው የአይሁድ ሥርዓት ከሕዝቡ መካከል የተመረጡ ሰባ አባላት የሚገኙበት ከፍ ተኛው የፍርድ ችሎት ነው ፤ የዚህ ሸንጎ ሊቀ መንበር ሊቀ ካህናቱ ነበር (ማቴ. 26 ፡59) ።

ሽማግሌዎች ፡- በብሉይ ኪዳን በጉሳ ፥ በነገድ ወይም በሕዝብ ዘንድ ተደማጭነት ላላቸው ሰዎች የተሰጠ ስም ነው ፤ በአዲስ ኪዳን "ሽማግ ሌዎች" በመባል የሚታወቁት ሦስት የተለያዩ ደረጃዎች ናቸው ፡- 1. በአራቱ መንጌላት ውስጥ "ሽማግሌዎች" የሚባሉት የታወቁ የአይሁድ መንፈሳውያን መሪዎች ናቸው ፤ ከእነርሱም መካ ከል አንዳንዶቹ የሸንጎ አባላት ነበሩ ። 2. በሐ.ሥ. 11-21 እንዲሁም በመልእክታት ውስጥ "ሽማግሌዎች" የሚባሉት የቤተ ክርስቲ ያን መሪዎች ናቸው ። 3. በዮሐንስ ራእይ "ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች" በመንግሥተ ሰማይ በእግዚ አብሔር ዙፋን ዙሪያ የሚገኙ ናቸው ።

ቃልኪዳን ፡- በሰውና በሰው ወይም በእግዚአብሔ ርና በሰው መካከል የሚደረግ የጋራ ስምምነት ነው ፤ እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር (ዘፍ. 9 ፥8-17) ቀዋሎም ከአብርሃም ጋር (ዘፍ. 17 ፥1-8) ቃል ኪዳን ገባ ፤ ይሁን እንጂ በብሉይ ኪዳን አብዛኛ ውን ጊዜ ቃል ኪዳን የሚያመለክተው በሙሴ ጊዜ በእግዚአብሔርና በእስራኤል ሕዝብ መካ ከል የነበረውን ስምምነት ነው (ዘጸ. 24 ፥4-8) ።

ቄሳር ፡- በጥንት ጊዜ ለሮም ንጉሠ ነገሥት ይሰጥ የነበረ የማዕርግ ስም ነው ።

ቅድስተ ቅዱሳን ፡- ከተቀደሱት የተቀደሰች ወይም ከተለዩት የተለየች የቤተ መቅደስ ውስጣዊ ሦስ ተኛው ክፍል ፤ የቃል ኪዳኑ ታቦትና የቀሩት ነዋያተ ቅድሳት የሚገኙበት ነው ፤ ሊቀ ካህናቱ ብቻ በዓመት አንድ ጊዜ በኃጢአት ስርየት ቀን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል ። "ቅድስት" የተቀ ደሰች ወይም የተለየች ማለት ሲሆን ፥ የቤተ መቅደሱ ሁለተኛ ክፍል ነው ።

ቡል ፡- በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር ስምንተ ኛው ወር ነው ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር የጥቅምት ወር መሆኑ ነው ።

ቢረሌ ፡- አረንጓዴ ወይም ወደ ሰማያዊ የሚያደላ አረንጓዴ ቀለም ያለው የከበረ ድንጋይ ነው ።

ባዓል ፡- በጥንት ጊዜ ከነዓናውያን ያመልኩት የነ በረ ጣዖት ፤ ይህም ጣዖት ልምላሜንና ዘርን ያስ ገኛል ተብሎ ይታመንበት ነበር ፤ ዕብራውያን በድል አድራጊነት ከነዓንን ከያዙ በኋላ ፥ ከእነ ርሱ ብዙዎቹ ባዓልንና የእርሱ መሰል የሆነች ውን አሼራን ማምለክ ጀመሩ ።

ብርጉድ ፡- ቀረፋ የሚመስል ፥ ከዛፍ ቅርፊት የሚ ገኝ ፥ ጥሩ ሽታ ያለው ቅመም ።

ብዔልዜቡል ፡- በአዲስ ኪዳን የርኵሳን መናፍስት አለቃ ለሆነው ለዲያብሎስ የተሰጠ ስም ነው ።

ታቦት ፡- በብሉይ ኪዳን ዘመን ከግራር እንጨት ተሠርቶ በወርቅ የሚለበጥ ሣጥን መሰል ነገር ነው ፤ ወሥርቱ ትእዛዛት የተጻፉባቸው ሁለቱ ጽላ ቶች በውስጡ ይቀመጡ ነበር ፤ "የቃል ኪዳን ታቦት" በመባልም ይታወቃል ።

ቴቤት ፡- በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር ዐሥረ ኛው ወር ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር የታሕ ሣሥ ወር መሆኑ ነው ።

ቶጻዚዮን (ወራውሬ) ፡- ቀለሙ ቢጫ የሆነ የሚያ ብለጨልጭ የከበረ ድንጋይ ነው (ዘጸ. 28 ፥17 ፤ ራእ. 21 ፥20) ።

ኒሳን ፡- በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር የመጀመሪ ያው ወር ነው ፤ ይህ ወር አንዳንድ ጊዜ "አቢብ" ይባላል ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ሚያዚያ መሆኑ ነው ።

ናርዶስ ፡- ከተክል የሚገኝ ውድ የሆነ ሽቶ ።

ናዝራዊ ፡- 1. የናዝሬት ከተማ ተወላጅ የሆነ ሰው ፤ 2. የተቀደሰ ወይም የተለየ ማለት ነው ፤ ሰው ናዝ ራዊ ሲሆን ከሚያስክር መጠጥ ፥ ጠጕርን ከመላጨ ትና ሬሳ ከመንካት ራሱን ይከላከል ነበር ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ናዝራዊ" ተብሎ ቢጠራም ፥ ይህ በናዝሬት ማደጉን እንጂ በኦሪት ሕግ መሠረት ናዝራዊ መሆኑን አያመለክትም (ማቴ. 1 ፥23) ፤ የጥንት ክርስቲያኖችም አንዳንድ ጊዜ "ናዝራው ያን" ይባሉ ነበር (ሐ.ሥ. 24 ፥5) ።

አልባስጥሮስ ፡- እንደ አበባ ማስቀመጫና እንደ ሽቶ ብልቃጥ የመሰለለ ልዩ ልዩ የከብር ዕቃ የሚሠራበት ነጭ ድንጋይ ።

አሜቴስጢኖስ ፡- ሐምራዊ ቀለም ያለው የከበረ ድንጋይ ።

አሜን ፡- በዕብራይስጥ "የተረጋገጠና የታመነ" የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን "ይሁን" "በእ ውነት" ማለት ነው ፤ ክርስቶስ እውነት ስለ ሆነ "አሜን" የሚል ስም ተሰጥቶታል (ራእ. 3 ፥14 ፤ 2 ቆሮ. 1 ፥20) ።

አረማውያን ፡- በጥንት ጊዜ አይሁዳውያን ያልሆኑ ሁሉ የሚጠሩበት ነው ። አሕዛብም ተብለው ይጠራሉ ።

አርዮስጋነስ ፡- የግሪክ ዋና ከተማ በሆነችው በአ ቴና የሚገኝ ኮረብታ ነው ፤ በዚህ ኮረብታ ላይ የከ ተማው ምክር ቤት አባሎች ከጥንት ጀምሮ ይሰበ ሰቡ ነበር ፤ እዚያ መሰብሰብ ከቀረ በኋላም "አር ዮስጋነስ" ለጉባኤው የተሰጠ ስም ሆኖአል ።

አርጤሚስ ፡- በተለይ በምዕራብ እስያ ትመለክ የነ በረች የጣዖት ስም ነው ፤ ይህች ጣዖት ልምላ ሜና ዘር ታስገኛለች ተብሎ ይታመንባት ነበር ።

አስታርቴ ፡- በጥንት ጊዜ በምዕራብ እስያ ትመለክ የነበረች ጣዖት ናት ፤ ይህችም ጣዖት ልምላሜ ንና ዘርን ፥ በጦርነትም ጊዜ ድልን የምታስገኝ ነች ተብሎ ይታመንባት ነበር ።

አሼራ ፡- ከነዓናውያን ያመልኳት የነበረች ጣዖት ናት ፤ ይህችም ጣዖት ልምላሜና ዘር ታስገኛለች ተብሎ ይታመንባት ነበር ፤ ዕብራውያን በድል አድራጊነት ከነዓንን ከያዙ በኋላ ከእነርሱ ብዙ ዎቹ አሼራንና የእርስዋ መሰል የሆነውን ባዓልን ማምለክ ጀመሩ ።

አቢብ ፡- በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር የመጀመሪ ያው ወር ነው ፤ ይህ ወር አንዳንድ ጊዜ "ኒሳን" ይባላል ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ሚያዝያ መሆኑ ነው ።

አዳር ፡- በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር ዐሥራ ሁለ ተኛው ወር ነው ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር መጋቢት መሆኑ ነው ።

ኡሪምና ቱሚም ፡- ሊቀ ካህናቱ በሚለብሰው በኤ ፉዱ ላይ ባለው የደረት ኪስ ውስጥ የሚከተቱ ሁለት ዕቃዎች (ዘጸ. 28 ፥30) ፤ ካህናት በኡሪ ምና ቱሚም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይጠይቁ ነበር (ዘጸ. 27 ፥21) ።

ኢታኒም ፡- በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር ሰባተ ኛው ወር ነው ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ጥቅምት መሆኑ ነው ።

ኢያሰጲድ ፡- ቀለሙ ልዩ ልዩ የሆነ የከበረ ድን ጋይ ነው ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው ኢያስ ጲድ ቀለሙ አረንጓዴ ወይም ጥርት ያለ ቀለም ያለው ነው ።

ኤሎል ፡- በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር ስድስተ ኛው ወር ነው ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር የመስከረም ወር መሆኑ ነው ።

ኤፉድ ፡- በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናቱ መሥዋዕት በሚያቀርብበት ጊዜ በደረቱ ላይ የሚለብሰው የልብስ ዐይነት ነው ።

ኤፒኩሮሶች ፡- "ኤፒኩረስ" የተባለውን ጻግሪክ ፈላስፋ ትምህርት የሚከተሉ ሰዎች ናቸው ፤ ኤፒኩረስ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ341-270 ዓመተ ዓለም ገደማ የነበረ ነው ፤ ኤፒኩረስ ያስተማረውም "በሰው ሕይወት ከፍተኛውን ቦታ መያዝ የሚገባው ደስታ ነው" በማለት ነበር ።

ኤስቶይኮች ፡- "ዜኖ" የተባለውን የግሪክ ፈላስፋ ትምህርት የሚከተሉ ሰዎች ናቸው ፤ ዜኖ ከክርስ ቶስ ልደት በፊት ከ334-265 ዓመተ ዓለም ገደማ የነበረ ነው ፤ ዜኖ ያስተማረውም "ደስታ የሚገኘው ከሥጋዊ ፍትወትና ከሥቃይ ነፃ በመ ሆን ነው" በማለት ነበር ።

እንስላል ፡- ቅርንጫፉ ፥ ቅጠሉና ዘሩ ለቅመምነት የሚያገለግል ትንሽ ተክል ።

እግዚአብሔር ፡- በዕብራይስጥ "ያህዌህ" ወይም በአንዳንድ ትርጉም "ይሆዋ" የሚለውን ስም ያመለክታል ። በአማርኛ የፍጥረት ሁሉ ጌታ መሆኑን ያመለክታል ።

እርዮን ፡- በክረምት ወራት በምሽት በሰማይ ላይ የሚታይ አንጸባራቂ የሆነ የከዋክብት ክምችት ።

ከሙን ፡- ዘሩ ተፈጭቶ ለቅመምነት የሚያገለግል ትንሽ ተክል ነው ።

ከርቤ ፡- ጥሩ ሽታ ያለው ከእንጨት ላይ የሚገኝ መራር ሙጫ ፥ በመድኀኒትነትም ያገለግላል (ማር. 15 ፥23) ፤ አይሁዳውያን ሬሳ ያሹበት ነበር (ዮሐ. 19 ፥39) ።

ኪሩቤል ፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ሰማያውያን ፍጥረቶች ።

ኪስሌው ፡- በዕብራውያን ዘመን አቈጣጠር ዘጠነ ኛው ወር ነው ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር ታሕሣሥ ወር መሆኑ ነው ።

ኬልቄዶን ፡- ልዩ ልዩ ቀለም ያለው የከበረ ድን ጋይ ።

ክርስቲሎቤ ፡- አብዛኛውን ጊዜ ጥርት ያለ ቀለም ያለው የከበረ ድንጋይ ነው ።

ክርስቶስ ፡- መጀመሪያ የማዕርግ ስም ነበር ፤ በዕብ ራይስጥ "መሲሕ" የተባለው በግሪክ "ክርስቶስ" ተብሎአል ፤ ትርጉሙም "የተቀባ" ማለት ነው ፤ ኢየሱስ "ክርስቶስ" የተባለው እግዚአብ ሔር የመረጠውና አዳኝና ጌታ አድርጎ የሳከው በመሆኑ ነው ።

ክርስጵራስስ ፡- ቀለሙ ግራጫ የሆነ የከበረ ድንጋይ ነው ።

ዘዩስ ፡- ከግሪኮች አማልክት ዋና ሆኖ የሚቆጠር ጣዖት ነው ።

ዚፍ ፡- በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር ሁለተኛው ወር ፤ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ግንቦት ወር መሆኑ ነው ። የጋጢአት ማስተስረያ ቀን ፡- ከእስራኤላውያን በዓላት ሁሉ እጅግ የተከበረ ቀን ነው ፤ በዚህ ቀን ሊቀ ካህናቱ ለመላው የእስራኤል ሕዝብ ኃጢአት ማስተስረያ የሚሆን መሥዋዕት ያቀርባል (ዘሌ. 16) ፤ በዓሉም የሚከበረው በዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር ሰባተኛው ወር በገባ በዐሥረኛው ቀን ነው ፤ ይህም በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በመስከረም ሃያ አካባቢ ላይ መሆኑ ነው ፤ አይሁዳውያን ይህን ቀን "ዮም ኪፑር" ብለው ይጠሩታል ።

የአዲስ ጨረቃ በዓል ፡- እስራኤላውያን አዲስ ጨረቃ በታየች ቅጥር የሚያከብሩት ሃይማኖታዊ በዓል ነው ።

የዳስ በዓል ፡- የመከር ጊዜ እንዳበቃ ወዲያውኑ በአይሁዳውያን የሚከበር በዓል ነው ፤ በዚህ በዓል ሰሞን እስራኤላውያን ዳስ ሠርተው በውስጡ ይቀመጣሉ ፤ ይህም የሚያሳስባቸው የቀድሞ አባቶቻቸው በምድረ በዳ የተንከራተቱባቸውን ዘመናት ነው ፤ አይሁዳውያን ይህን በዓል "ሱኮት" ይሉታል ።

ያክንት ፡- ቀለሙ ሰማያዊ ወይም ወደ ሰማያዊ የሚያደላ አረንጓዴ የሆነ የከበረ ድንጋይ ።

ደቀ መዝሙር ፡- የሃይማኖት ትምህርት ተከታይ ወይም ተማሪ ማለት ነው ፤ በአዲስ ኪዳን "ደቀ መዝሙር" የሚለው ቃል አጥማቂው ዮሐንስን ወይም ኢየሱስን ይከተሉ ለነበሩት ሰዎች የሚሰጥ ስም ነበር ፤ ምእመናንም "ክርስቲያን" በሚል ስም ከመጠራታቸው በፊት "ደቀ መዝሙርት" ተብለው ይጠሩ ነበር ። (ሐ.ሥ. 11 ፡26)

ድብ ፡- ትልቅና አስፈሪ የሆነ የአውሬ ስም ነው ፤ "ታላቅ ድብና ታናሽ ድብ" ከምድር ወገብ በሰሜናዊ አቅጣጫ በሰማይ ላይ የሚታዩ ሁለት የከዋክብት ክምችቶች ናቸው ፤ በትንሹ ድብ ጅራት መጨረሻ ላይ የሚታየው ኮከብ "ፖላሪስ" ወይም "የምድር ጫፍ ኮከብ" ይባላል ።

ጃንደረባ ፡- ቃሉ ሁለት ትርጉም አለው ፤ 1. ከፍ ባለ ማዕርግ የሚገኝ ጠባቂ ፤ 2. ሰልብ ሰው ።

ጥሩር ፡- ከቁዳ ወይም ከብረት የሚሠራ ፤ ደረትን ወይም ጀርባን ከፍላጻ ወይም ከሰይፍ ለመከላከል የሚረዳ የጦር ዕቃ ነው ።

ጰንጠቆስጤ ፡- እስራኤላውያን በስንዴ መከር ጊዜ የሚያከብሩት "የመከር በዓል" ነው ፤ በግሪክ ቋንቋ "የጰንጠቆስጤ ቀን" ይባላል ፤ በዓሉ የሚከበረው የፋሲካ በዓል ባለፈ በኀምሳኛው ቀን በመሆኑ "ጰንጠቆስጤ" ተባለ ፤ ምክንያቱም "ጰንጠቆስጤ" በግሪክ ቋንቋ "ኀምሳኛ" ማለት ስለሆነ ነው ። ይህ ቀን መንፈስ ቅዱስ በጢተ ክርስቲያን ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በኀይል የወረደበት ዕለት ነው ። ይህም ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ኀምሳኛው ቀን መሆኑ ነው ።

ጸናጽል ፡- ከነሐስና ከብር ከሌላም የሚሠራ የዜማ ዕቃ ፤ እንዲንሸዋሸው የነሐስም ሆነ የብረት ቅጠል ይደረግበታል ፤ ለእግዚአብሔር ክብርም ይዘመርበታል ።

ጽዮን ፡- አያሩሳሌም ከተሠራችባቸው ተራራዎች አንዱ ነው ፤ ቃሉ "አምባ" ማለት ነው ።

ፈረያን ፡- በጥንት ጊዜ ለግብጽ ነገሥታት ይሰጥ የነበረ የማዕርግ ስም ነው ።

ፈሪሳውያን ፡- ከአይሁድ ሃይማኖት ወገኖች አንዱ ክፍል ናቸው ፤ እነርሱም ሙሴ ሕግና ከዘመናት በኋላ የተጨመሩትን ልዩ ልዩ ትእዛዝና ሥርዓት በመጠበቅና በማስጠበቅ እጅግ ጠንቃቃዎች ነበሩ ።

ፋሲካ ፡- እስራኤላውያን በየዓመቱ የኒሳን ወር በገባ በ14ኛው ቀን የሚያከብሩት በዓል ነው ፤ በዚህ በዓል ዕብራውያን ከግብጽ ባርነት ነፃ መውጣታቸውንም ያስታውሳሉ ፤ የሞት መልአክ የግብጻውያንን የበኩር ልጆች በገደለ ጊዜ የዕብራውያንን ቤቶች እያለፈ ሄዶአል (ዘጽ. 12 ፡23-27) ፤ በአይሁድ ይህ በዓል "ፔሳሕ" ይባላል ፤ ትርጉሙም "ማለፍ" ማለት ነው ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ሳምንት የፋሲካ ሳምንት ነበር ፤ እርሱም ንጹሕ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ይሙን ስላፈሰሰልን "ፋሲካችን ክርስቶስ" ተብሎአል ፤ ስለዚህ የክርስቶስ ትንሣኤ በዓልም "ፋሲካ" ተብሎ ይጠራል ።

ፕሊያደስ ፡- በክረምት ወራት በሰማይ ላይ የሚታይ የከዋክብት ክምችት ነው ፤ በአንዱ ክምችት ሰባት ከዋክብት ይገኙበታል ።

ፕሪም ፡- አይሁዳውያን በየዓመቱ የአዳር ወር በገባ በ14ኛው ቀን የሚያከብሩት ሃይማኖታዊ በዓል ነው ፤ በዚህ በዓል አስቴርና ሞርዶክዮስ አይሁዳውያንን ከሐማን እጅ ማዳናቸውን ያስታውሳሉ ፤ ታሪኩ በአስቴር መጽሐፍ ይገኛል ።

የቃላት ንጽጽር

በወዲሱ ትርጉም	በዕብራይስጥ	በ1954 ዕትም
ሄኖስ	ኤኖሽ	
ሆሴዕ	ሆሼዓ	
ሊባኖስ	ለባኖን	
ላሜክ	ላሜሕ	
ሎዛ	ሉዝ	
ሐሴቦን	ሔሽቦን	
ሐጌ	ሐጋይ	
ሑር	ሖር	
ሒልቂያ	ሒልቂያ	ኬልቅያስ
ሔርሞን	ሔርሞን	ዓርሞንኤም
ሔዋን	ሕዋ	
ሕልቃና	ኤልቃና	
ሕዝቅኤል	ይሔዝቅኤል	
ሕዝቅያስ	ሒዝቂያ(ሁ)	
መርዶክዮስ	ሞርደካይ	
ሚርያም	ሚርያም	ማርያም
ሚሳቅ	ሜሻክ	
ሚካያ	ሚካያ	ሚከያስ
ሚከያስ	ሚካ	
መላልኤል	ማህላልኤል	
ማቱሳላ	መቱሼላሕ	
ማኑሄ	ማኖሕ	
ምድያም	ሚድያን	
ሣፋጥ	ሻፋጥ	
ሜት	ሼት	
ረዓብ	ራሕብ	
ራምሴ	ራዕመሴስ	
ሮቤል	ረኡቤን	
ሮብዓም	ረሕብዓም	
ሰላትያል	ሸአልቲኤል	
ሰራጵታ	ጻርፋት	
ሰናከሬብ	ሳንሔሪብ	
ሲሖን	ሲዮን	
ሲማራ	ሲሰራ	
ሲድራቅ	ሻድራክ	
ሲዶና	ጻዶን	
ሳምሶን	ሺምሾን	ሶምሶን
ሳሮን	ሻሮን	
ሳዶቅ	ጻዶቅ	
ሳፋን	ሻፋን	
ሴሎ	ሺሎ	
ሴም	ሼም	
ሴኬም	ሼኬም	

በወዲሱ ትርጉም	በዕብራይስጥ	በ1954 ዕትም
ሴዴቅያስ	ጻድቂያ	
ሶፎንያስ	ጻፋንያ	
ቀሃት	ቀህት	ቀዓት
ቀርሜሎስ	ካርሜል	
ቂሮስ	ኮሬሽ	
ቂስ	ቂሽ	
ቃየል	ቃይን	
ቃይናን	ቄናን	
ቃዴስ	ቃዲሽ	
ቄዴሽ	ቄዲሽ	ቃዴስ
ቄድሮን	ቂድሮን	
ቆራሕ	ቆራሕ	ቆሬ
በራክያ	ቤሬክያ	
ቢያር	በያር	
ባላ	ቢልሃ	
ባሳን	ባሻን	
ባቢሎን	ቬጎባር	ሰናዖር
ባዕሻ	ባዕሻ	በአሳ
ቤልሻጻር	ቤልሻጻር	ብልጣሶር
ቤርሳቤህ	በኤር ሼባዕ	ቤርሳቤህ
ቤርሳቤህ	ባትሼባዕ	ቤርሳቤህ
ቤትኤል	ቤትኤል	ቤቴል
ብልጣሶር	ቤልጠሻጻር	ብልጣሶር
ብንያም	ቢንያሚን	
ብዔልዜቡል	በዓልዘቡብ	
ቦዔዝ	ቦዓዝ	
ታራ	ታራሕ	
ትዕማር	ታማር	
ነህምያ	ነሔምያ	
ነአሶን	ናሕሾን	
ነዋ	ኑን	
ናሆም	ናሑም	
ናምሩድ	ኒምሮድ	
ናቡቴ	ናቦት	
ናቡከደነፆር	ነቡካድነጻር	
ናኮር	ናሖር	
ናዖሚ	ናዖሚ	ኑኃሚ
ናዖስ	ናሖሽ	
ንዕማን	ናዕማን	
ንፍታሌም	ናፍታሊ	
አልዓዛር	ኤልዓዛር	
አሒጦብ	አኪጦብ	
አሚናዳብ	አቢናዳብ	

በወዲሱ ትርጉም	በዕብራይስጥ	በ1954 ዕትም
አሜስያስ	አማጥያሁ	
አሞን	አሞን	አሞጽ
አሞጽ	ዓሞስ	
አሦር	አሹር	
አራራት	አራራጥ	
አርጤክስስ	አሐሸዊሮሽ	
አርፋክሳድ	አርፓክሻድ	
አሴር	አሼር	
አስራዶን	ኤሳርሐዶን	
አስቀሎና	አሽቀሎን	
አስቴር	ኤስቴር	
አስጢን	ዋሽቲ	
አቢሜሌክ	አሒሜሌክ	
አቢሜሌክ	ዓቢድ ሜሌክ	
አቤሮን	አቢራም	
አቤሴሎም	አብሻሎም	
አብርሃም	አብራሃም	
አብደናጎ	ዐቢድነጎ	
አብድዩ	ዖባድያ	
አኪጦፌል	አሒቶፌል	
አካዝ	አሐዝ	
አካዝያስ	አሐዝያሁ	
አዶንያስ	አዶኒያ	
አጋር	ሃጋር	
አሳይያስ	የሻዕያሁ	
አዩኤል	ዮኤል	
አያሱ	የሆሹዓ	
አያቡሳው	የቡስ	
አያቡስቴ	ኢሽቦሼት	
አይዝራኤል	ይዝራዕኤል	
አዮሣፍጥ	ይሆሻፋጥ	
አዮራም	ይሆራም	
አዮራም	ዮራም	
አዮርብዓም	ያሮብዓም	
አዮስያስ	ዮሺያ	
አዮቤድ	ዖቤድ	
አዮናዳብ	ዮናዳብ	
አዮአሐዝ	ዮአሐዝ	
አዮአቄም	ይሆያቂም	
አዮአብ	ዮአብ	
አዮአታም	ዮታም	
አዮአካዝ	ይሆአሐዝ	
አዮኤል	ዮኤል	
አዮዴቅ	ይሆጻዳቅ	
አልሳዕ	ኤሊሻዕ	

በወዲሱ ትርጉም	በዕብራይስጥ	በ1954 ዕትም
አልዛቤል	ኢዜቤል	
አልያስ	ኤሊያ(ሁ)	
አልያቂም	ኤልያቂም	
አቤንዔዜር	ኤቤንዔዜር	አቤንኤዘር
አሴይ	ዩሻይ	
አስክንድር	– – –	አስክንድሮስ
አስጥን	ተርሴስ	ተርሴስ
አርዮን	ኡሪያ	
ኪራም	ሒራም	
ካም	ሓም	
ካራን	ሐራን	
ኬሊዎን	ኪልዮን	
ኬብሮን	ሔብሮን	
ዐማሌቅ	ዐማሌቅ	አማሌቅ
ዐስታሮት	ዓሽታሮት	
ዓሞጽ	ዓሞጽ	አሞጽ
ዔባል	ዔባል	ጌባል
ዔጽዮንጋብር	ዔጽዮንጌቤር	
ዕዝራ	ዔዝራ	
ዖባድያ	ዖባድያ	አብድዩ
ዖዝያን	ዑዚያ	
ዖግ	ዖግ	ዐግ
ዘካርያስ	ዘካርያ	
ዛብሎን	ዝቡሎን	
የትሮ	የትሮ	ዮትሮ
ዩሁ	ዩሁ	ኢዩ
ይፉኔ	ይፉኔ	ዮፍኒ
ዮናስ	ዮና	
ዮአኪን	ዮያኪን/የሆያኪን	
ዮዳሄ	ይሆያዳዕ	
ዮፍታሔ	ይፍታሕ	
ዶይቅ	ዶኤግ	
ገለዓድ	ጊልዓድ	
ገሪዛን	ገሪዚም	
ገባዖን	ጊበዖን	
ጋት	ጋት	ጌት
ጌልገላ	ጊልጋል	
ጌሜም	ጎሼን	
ጌዴዎን	ጊድዮን	
ግዮን	ጊሖን	
ጎልያድ	ጎልያት	
ጣፍናስ	ታሕፋንሔስ	
ፋሬስ	ፌሬጽ	
ፋቁሔ	ፈቃሕ	
ፐዖር	ፐዖር	ፌጎር